# ኢትዮጵያና፡ ምዕራባዊ፡ ሥልጣኔ

ከከበደ ፡ ሚካኤል ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፵፮ ዓ. ም.

ተቀንቅመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፲ቱ ፡ ወ፱ቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡
ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ። ፴—፮—፵፮ ቁ. ፩፻፳፩ ፡

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡

አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

በደግነታቸው ፡


መልካም ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሆኖ ፡

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲቀበሉት ፡

ጥልቅ ፡ በሆነ ፡

ትሕትና ፡ እየለመነ ፡

ደራሲው ፡ ያበረክታል ።



# ኢ ት ዮ ጵ ያ ና ፡

# ም ዕ ራ ባ ዊ ፡ ሥ ል ጣ ኔ ።

ብርሃን ፤ ብርሃን ፤ አሁንም ፡ ብዙ ፡ ብርሃን !

ጎ ቴ ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ሲጽፍ ፡ የደራሲው ዋና ፡ አሳብ ፤ ባገራችን ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የምዕራባውያን ፡ ሕዝቦች ፡ ሥልጣኔ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማነኛውም ፡ ተራ ፡ አን ባቢ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲያውቀውና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችም ፡ አዲሲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቷ ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መሪነት ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመራመድ ፡ የምታደርገውን ፡ መጣጣር ፡ ለመረዳት ፡ እንዲችሉ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ብርሃን ፡ እንዲሆንላቸው ፡ ነው ።

ከደራሲው ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንዳያሳትም ፡ ክልክል ፡ ነው ።

COPYRIGHT

ማውጫ ።　　　　　　　　　　　　ገጽ ።


| | |
|---|---|
| የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰዎች ፡ | ፲፬ |
| የመንግሥታት ፡ መቋቋም ፡ | ፲፯ |
| የባርነት ፡ ትርጉም ፡ | ፲፱ |
| እስራኤላውያን ፡ | ፳፫ |
| ሆሜር ፡ | ፳፭ |
| ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ | ፳፱ |
| የግሪክ ፡ ፈላስፎች ፡ | ፴፩ |
| ባሮች ፡ በግሪኮች ፡ ዘንድ ፡ | ፴፰ |
| ሮማውያን ፡ | ፵፩ |
| ባሮች ፡ በሮማውያን ፡ ዘንድ ፡ | ፵፬ |
| የሮማ ፡ መውደቅ ፡ | ፵፯ |
| የግሪኮችና ፡ የሮማውያን ፡ እምነት ፡ | ፵፰ |
| የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ | ፶ |
| መካከለኛው ፡ ዘመን ፡ | ፶፫ |
| ባርነት ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ | ፶፯ |
| ዳግም ፡ ልደት ፡ | ፷ |
| ባሮች ፡ በሜርካ ፡ አገር ፡ | ፷፭ |
| የሄዱበት ፡ ሁኔታ ፡ | ፸፩ |
| ባርነትን ፡ ለማስወገድ ፡ የተደረገ ፡ የመንፈስ ፡ ትግል ፡ | ፸፬ |
| ሊንኮልን ፡ | ፹፫ |
| መሠረት ፡ የሌለው ፡ ክስ ፡ | ፹፯ |
| ባለፈው ፡ ዘመን ፡ ጉዳዩ ፡ ስላለመፈጸሙ ፡ | ፺፩ |
| ባርነት ፡ ባዬ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ስለመወገዱ ፡ | ፺፭ |
| ግ. ቀ. ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የፈጸሙዋቸው ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራዎች ፡ | ፺፰ |
| የሁከት ፡ ዘመን ፡ | ፻፲፱ |
| የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፡ | ፻፴ |
| ታላላቅ ፡ የጥበብ ፡ ሰዎች ፡ | ፻፴፰ |
| መደምደሚያ ፡ | ፻፵፯ |

## ማረሚያ ።

በገጽ ፡ ፳፯ ፡ በ፲፬ኛው ፡ መስመር ፡ «ይህን ፡ በደል ፡ ለመቀበል ፡ » የሚለውን ፡ ቃል ፡ « ይህን ፡ በደል ፡ ለመበቀል ፡ » ብሎ ፡ ማንበብ ፡ ነው ።

በገጽ ፡ ፵፫ — በ፲ኛ ፡ መስመር ፡ «አቴንና ፡ » የሚለውን ፡ ቃል ፡ » አቴናን ፡ » ብሎ ፡ ማንበብ ፡ ነው ።

በገጽ ፡ ፸፩ — በ፳፫ኛ ፡ መስመር ፡ « በጭራሽ ፡ ስለሚያስቡላቸው ፡ » የሚለውን ፡ « በጭራሽ ፡ ስለማያስቡላቸው ፡ » ብሎ ፡ ማንበብ ፡ ነው ።

በገጽ ፡ ፻፳፫ — በ፳ኛ ፡ መስመር ፡ «ኢይጠረጥርም ፡ » የሚለውን ፡ «አይጠረጠርም ፡ ብሎ ፡ ማንበብ ፡ ነው ።

በገጽ ፡ ፻፴፯ — በ፲፫ኛ ፡ መስመር ፡ «ይህም ፡ ሁኔታ ፡ ሞንቴስኪዩ ፡ . . . » የሚለውን ፡ « ይህም ፡ ሁኔታ ፡ ስናስተውለው ፡ ሞንቴስኪዩ ፡ . . . » ብሎ ፡ ማንበብ ፡ ነው ።

በገጽ ፡ ፻፵፫ — በ፲፭ኛ ፡ መስመር ፡ ከናል ፡ ደ. ሱዌዝ ፡ የተከፈተበትን ፡ ዘመን ፡ » ፲፰፻፶፱ ፡ ዓ. ም. » ብሎ ፡ ማንበብ ፡ ነው ።

---

## ማሳሰቢያ ።

፩ኛ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኝ ፡ የዘመን ፡ ቊጥር ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ስለሆነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ የዘመን ፡ አቆጣጠር ፤ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ እንዳገራችን ፡ የዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ መሆኑን ፡ እናሳስባለን ።

፪ኛ ፡ የትሮይ ፡ ከተማ ፡ ስለጠፋችበት ፡ ዘመን ፡ በገጽ ፡ ፳፯ ፡ ስለተነገረው ፡ የዘመን ፡ ቊጥር ፡ « ስለ ፡ ዓለም ፡ ታሪክ ፡ ንግግር ፡ » የተባለውን ፡ የቦሱዬን ፡ መጽሐፍ ፡ መመልከት ፡ ነው ።

፫ኛ ፡ « የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፡ » በተባለው ፡ አርእስት ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኘው ፡ ሐተታ ፡ «ከፒቴኖች ፡ መናፍቃንና ፡ ሽፍቶች ፡ » የተባለውን ፡ ከፈሎፕ ፡ ሚለር ፡ የተጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ በተለየ ፡ መመልከት ፡ ይቻላል ።

፬ኛ ፡ በገጽ ፡ ፻፴፫ ፡ ስለ ፡ ሙዚቃ ፡ የተጠቀሰው ፡ በሻኬስፒር ፡ ቴአትር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ቃል ፡ ሎሬንዞ ፡ ለጀሲካ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ላገራችን ፡ አንባቢዎች ፡ እንዲመች ፡ በማለት ፡ ለብዙዎች ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ ተደርጓል ።

## መቅድም ።

ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አብርሃ

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መሪነት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ የምታደርገው ፡ እርምጃ ፡ በሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋና ፡ ጉዳዩ ፡ በመሆኑ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሁሉ ፡ ጥቅሙንና ፡ ዋጋውን ፡ ዐውቀው ፡ በመንፈሳቸውና ፡ በዕለታዊ ፡ ተግባራቸው ፡ መተባበርና ፡ መሥራት ፡ እንደሚገባቸው ፡ ተረድተውታል ። ይህም ፡ አስተያየትና ፡ አያያዝ ፡ የተሟላ ፡ እንዲሆን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንድታገኘው ፡ የሚጥሩበት ፡ ሥልጣኔ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከምናውቀው ፡ አብልጠን ፡ ለመረዳት ፡ መመራመር ፡ ያሻናል ።

ኢትዮጵያ ፡ ከዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ ሳትገናኝ ፡ ተለያይታ ፡ መንገዱ ፡ ታጥሮባት ፡ የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመከፈል ፡ ሳትችል ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከቈየች ፡ በኋላ ፡ ያውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ኃይላቸውና ፡ ሥልጣኔያቸው ፡ ተስፋፍቶ ፡ የሱዌዝም ፡ የባሕር ፡ በር ፡ ተከፍቶ ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ የህንድ ፡ መንገድ ፡ መሆን ፡ ሲጀምር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ ተቀራርባ ፡ መገናኘት ፡ ጀመረች ።

ይህም ፡ ስለተባለ ፡ ካናል ፡ ደሱዌዝ ፡ በመከፈቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ልትጠቀምበት ፡ ይገባት ፡ የነበረውን ፡ ያህል ፡ እንዳልተጠቀመች ፡ መዘንጋት ፡ አይገባንም ። ምክንያቱም ፡ ከባሕር ፡ ጋር ፡ የሚያገናኛት ፡ ጠረፍ ፡ ዙሪያውን ፡ በሦስቱ ፡ ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ማለት ፡ በእንግሊዝ ፡ በፈረንሣይና ፡ በኢጣሊያ ፡ ስለተያዘባት ፡ ካለም ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ የማትችል ፡ በሩ ፡ የተዘጋባት ፡ እሥረኛ ፡ በመሆኗ ፡ ነው ። ለወደፊቱም ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ካልተሻሻለላት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ የምታደርገው ፡ እርምጃ ፡ አይቃናላትም ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ በታላላቆች ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ ችላ ፡ የተባለው ፡ ይህ ፡ ችግርዋና ጉዳቷ ፡ አሁን ፡ በሚደረገው ፡ ያለም ፡ መንግሥታት ፡ ጉባኤ ፡ ተጠንቶ ፡ እንዲታወቅላትና ፡ ጥያቄዋ ፡ የሚገባውን ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያገኝ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

ሕዝብን ፡ ከፍ ፡ የሚያደርገው ፡ ሥልጣኔ ፡ መሆኑን ፡ በመመልከት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ያደረጉትን ፡ የጥበብ ፡ እርምጃ ፡ ለመከተል ፡ ስታስብ ፡ የሥልጣኔን ፡ መንፈስ ፡ ለመቀበል ፡ ባለበነ ፡ ፈቃድ ፡ ለመሆኗ ፡ ማስረጃ ፡ አድርጋ ፡ እንድትፈጽም ፡ የአውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ መጀመሪያ ፡ የጠየቋት ፡ ባርነትን ፡ ካገርዋ ፡ እንድታጠፋ ፡ ነው ። ኢትዮጵያም ፡ ይህንኑ ፡ አሳብ ፡ በመልካም ፡ አስተያየት ፡ ተቀበለች ። በየጊዜውም ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ ውል ፡ ተፈራረመች ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ልማድ ፡ ሆኖ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ የሚኖረውን ፡ ባርያ ፡ የመግዛትና ፡ የመሸጥ ፡ ንግድ ፡ በድካሙም ፡ በተገኘው ፡ ፍሬ ፡ የመጠቀምን ፡ ግፍ ፡ ለማስወገድ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አልነበረም ።

አውሮፓውያን ፡ ባርነትን ፡ ያስወገዱት ፡ በረጅም ፡ ዘመን ፡ በሥልጣኔ ፡ መንፈስ ፡ ከደረጉት ፡ እርምጃ ፡ የተነሣ ፡ አእምሮዋቸው ፡ በጉዳዩ ፡ ብዙ ፡ ከሠራበትና ፡ ከታገለበት ፡ በኋላ ፡ ነበር ። ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ በተጠየቀች ፡ ጊዜ ፡ ሌሎቹ ፡ መንግሥታት ፡ በብዙ ፡ ዘመን ፡ የፈጸሙትን ፡ ሥራ ፡ እሷ ፡ በቶሎ ፡ እንድትፈጽመው ፡ ስለ ፡ ተጠየቀች ፡ ይህን ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ አቅቷት ፡ በሁከት ፡ ላይ ፡ ሳለች ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አስደናቂ ፡ የሆነ ፡ ትጋታቸውንና ፡ ለዘመኑ ፡ ትግል ፡ አስፈላጊ ፡ የነበረውን ፡ ቈራጥነታቸውን ፡ ይዘው ፡ ደረሱላት ።

ዛሬ ፡ ሲመለከቱት ፡ ባርነት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በመወገዱ ፡ የተሠራው ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የሚያስደንቅና ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ አይታያቸውም ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ስንት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ዕድሜያቸውን ፡ ሙሉ ፡ የደከሙበት ፤ ያሜሪካ ፡ ሕዝቦች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ የተዋጉበት ፤ በአውሮፓም ፡ የብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ አንጐል ፡ ከደከመበትና ፡ ከታገለበት ፡ በኋላ ፡ እንዲወገድ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ትልቅ ፡ የመንፈስ ፡ ( ሬቮሊሲዮን ፡ ) መለዋወጥ ፡ የተፈጸመበት ፤ ሊንኮልንን ፡ የመሰለ ፡ ትልቅ ፡ ሰውም ፡ ሕይወቱን ፡ የሰዋበት ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፣ ስናስታውሰው ፡ ዓለም ፡ ከድንቁርና ፡



ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ በተራመደች ፡ ጊዜ ፡ ስለሰብአዊ ፡ መብት ፡ የተፈጸመው ፡ አንዱ ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ባርነትን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ለማጥፋት ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ የገጠማቸው ፡ ችግር ፡ ታላቅ ፡ እንደነበረ ፤ ከፍጻሜ ፡ በማድረሳቸውም ፡ ለአገራቸውና ፡ ለሕዝባቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ውለታ ፡ እንደሠሩላቸው ፡ በሙሉ ፡ ለመረዳት ፡ የምንችለው ፡ የባርነት ፡ ጉዳይ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ሁኔታ ፡ ስንረዳውና ፡ ስናስተውለው ፡ ነው ። ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ባርነት ፡ እንዲወገድ ፡ በመከራከራቸው ፡ ወይም ፡ አሳቡን ፡ ከፍጻሜ ፡ በማድረሳቸው ፡ ስማቸውን ፡ በታሪክ ፡ ለማስጠራት ፡ የበቃ ፡ ሥራ ፡ ሆኖ ፡ ተቆጥሮላቸዋል ። ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ግን ፡ ባርነትን ፡ ካገራቸው ፡ ማስወገድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሕዝባቸው ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚያገኝበትን ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ሠርተዋል ። አሁንም ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ባርነት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ከተወገደ ፡ ብዙ ፡ ጊዜው ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ወዲያው ፡ እንደያዙ ፡ ከፈጸሙዋቸው ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ ባርነትን ፡ ማስወገዳቸው ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ስለ ፡ ባርነት ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ የምንናገረው ፡ በታሪክ ፡ አኳኋን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የዕለት ፡ ጉዳያችን ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ። ባጭሩ ፡ በጠቅላላው ፡ በዓለም ፡ ላይና ፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባርነት ፡ እንዴት ፡ እንደተወገደ ፡ ታሪኩን ፡ ለመመልከት ፡ ስንል ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይልቁንም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አንባቢ ፡ ባርነት ፡ አሁንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገና ፡ ያልጠፋ ፡ እንዳይመስለው ፡ ስለ ፡ አላፊ ፡ ነገር ፡ የምንናገር ፡ መሆናችንን ፡ አስጠነቅቃለሁ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሚናገሩት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ዲስኩር ፡ ለሕዝባቸው ፡ የሚመኙለትና ፡ የሚደክሙለት ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ በትምህርት ፡ እንዲራመድ ፡ ለማድረግ ፡ መሆኑን ፡ ከመግለጥ ፡ አላቋረጡም ። ከዋና ፡ ተግባራቸውም ፡ አንዱ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ማስፋፋትና ፡ ተማሪዎችን ፡ መንከባከብ ፡ ማበረታታትም ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ለሕዝባቸው ፡ የሚሿት ፡ ይህች ፡ ሥልጣኔ ፡ ምንድነች ፡ ? ከወዴት ፡ መጣች ፡ ? ጠባይዋና ፡ ግብሩዋ ፡ ምንድነው ፡? እነሆ ፡ የእነዚህን ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ ለማወቅና ፡ ለመረዳት ፡ በጣም ፡ የተጣጣርን ፡ እንደሆን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ አሳብና ፡ ምኞት ፡ ተካፍለን ፡ የተለሙልንን ፡ መንገድ ፡ ተከተልን ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ።

የእነዚህን ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ መፈለግና ፡ መስጠት ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አይደለም ። እኔም ፡ በዚች ፡ ታናሽ ፡ መጽሐፍ ፡ እሞክራለሁ ፡ እንጂ ፡ ልፈጽመው ፡ አልችልም ። የበለጠ ፡ ሌላ ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ የጐደለ ፡ ነገር ፡ ይሞላለታል ። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ይህንኑ ፡ ለማወቅና ፡ የሥልጣኔን ፡ እውነተኛን ፡ መንገድ ፡ ለመያዝ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ መንፈስ ፡ የተነሣ ፡ ሆኖ ፡ ሲጓጓ ፡ መታየቱ ፡ ነው ።

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መሪነት ፡ ሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስትገባ ፡ በማየታችን ፡ እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሆን ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሊሰማን ፡ ይገባል ። በሁሉም ፡ ረገድ ፡ ታሪኳ ፡ የሚያኰራት ፡ አገር ፡ የሆነችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጐደላትን ፡ ሥልጣኔ ፡ ባገኘች ፡ ጊዜ ፡ ትልቅ ፡ መንግሥት ፡ እንደምትሆን ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ዓላማ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያገኝ ፡ ልጆቿ ፡ ጥበብን ፡ ለማግኘት ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ መጣር ፡ አለባቸው ።

ሥልጣኔ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ውብ ፡ ነገር ፡ ነች ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ መሥዋዕት ፡ ትጠይቃለች ። ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ካልሆነ ፡ አይገኝም ። ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለዚህ ፡ የጋራ ፡ ተግባር ፡ እያንዳንዱ ፡ በግል ፡ ጥረቱ ፡ ምን ፡ እንደፈጸመ ፡ ሕሊናውን ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ተግባሩን ፡ በተሰጠው ፡ ስጦታ ፡ እያቃና ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ ጥበብን ፡ በመሻትና ፡ ዕውቀትም ፡ በመጨመር ፡ ራሱን ፡ ማሻሻል ፡ አንዱ ፡ ዓይነተኛ ፡ አገልግሎት ፡ ነው ።

ክብሩንና ፡ ነፃነቱን ፡ ጠብቆ ፡ ለመኖር ፡ የሚቻልበት ፡ መንገድ ፡ በጥበብ ፡ ዘዴ ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ከጐረቤቱ ፡ በታች ፡ እንዳይሆን ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ በሚታገልበት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ኢትዮጵያን ፡ የመሰለ ፡ ለነፃነቷ ፡ ቀናተኛ ፡ የሆነች ፡ አገር ፡ ልጆችዋ ፡ ሊነቁ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።



እንግዲህ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈበትን ፡ አሳብ ፡ ስናጠቃልለው ፡ ባርነት ፡ እንዴት ፡ እንደተወገደና ፡ ሥልጣኔ ፡ ምን ፡ እንደሆነች ፡ ለመረዳት ፡ በየዘመኑና ፡ በየሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ያደረገችውን ፡ እርምጃ ፡ እየተከተልን ፡ የዓለምን ፡ ታሪክ ፡ አሁን ፡ እስካለንበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ለማስተዋል ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያትም ፡ የባርነትን ፡ ጉዳይና ፡ የሥልጣኔን ፡ ዜና ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ አድርገን ፡ እንመለከተዋለን ።

ባሮችን ፡ ነፃ ፡ ለማውጣትና ፡ የባርያንም ፡ ደንብ ፡ ለማሻሻል ፡ በየጊዜው ፡ ባገራችን ፡ ስለወጡት ፡ አዋጆች ፡ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ በገባርና ፡ ባገረ ፡ ገዢዎች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ሁኔታ ፡ በቸገረኝ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሙሉ ፡ እርዳታቸውን ፡ ስላደረጉልኝ ፡ ለክቡር ፡ አቶ ፡ ጉብረ ፡ ወልድ ፡ እንግዳ ፡ ወርቅ ፡ ምስጋናዬን ፡ እገልጣለሁ ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በፈረንሣይና ፡ በእንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ ሲተረጐም ፡ የረዱኝ ፡ ሙሴ ፡ ማርሴል ፡ ሃሲድ ፡ ምስተር ፡ ሉሲያን ፡ ማትና ፡ ምስተር ፡ክላረንስ ፡ ጌ ፡ ፔሪን ፡ አመሰግናለሁ ። ይልቁንም ፡ ሙሴ ፡ ማርሴል ፡ሃሲድ ፡ መጽሐፉ ፡ ሲታተም ፡ የማተሚያ ፡ ቤቱን ፡ [illegible] ፡ ስለረዱኝ ፡ ልዩ ፡ ምሥጋና ፡ ይገባቸዋል ።

## የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰዎች ።

እግዚአብሔር ፡ አዳምና ፡ ሔዋንን ፡ ሲፈጥራቸው ፡ በምድረ ፡ ገነት ፡ አስቀምጧቸው ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ በደሉት ፡ ሳይሠሩና ፡ ሳይደክሙ ፡ በደስታና ፡ በሲሳይ ፡ ከሚኖሩበት ፡ የጸጋ ፡ ቦታ ፡ አስወጥቶ ፡ ባባረራቸው ፡ ጊዜ ፡ መራብና ፡ መጠማት ፡ መታረዝና ፤ መታመም ፡ መጨነቅና ፡ መሞት ፡ ደረሰባቸው ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የሚኖሩትን ፡ ፍጡሮች ፡ ሁሉ ፡ ስንመለከት ፡ ሁሉም ፡ ረግተው ፡ ይኖራሉ ። ለምሳሌ ፡ እንስሳትን ፡ ስናስተውል ፡ ከምግባቸው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይፈልጉም ። ግማሾቹ ፡ ሣር ፡ ቅጠል ፡ ተመግበው ፤ ግማሾቹም ፡ ሥጋ ፡ በልተው ፡ ውሃ ፡ ጠጥተው ፡ ሲኖሩ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ የሚፈልጉትና ፡ የሚያምራቸው ፡ ነገር ፡ የለም ።

ሰው ፡ ግን ፡ ሲፈጠር ፡ ከእንስሳት ፡ ይልቅ ፡ የተጐዳ ፡ ሆኖ ፡ ይወለዳል ። ይኸውም ፡ በልብስ ፡ ረገድ ፡ ነው ። እንስሳት ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረላቸው ፡ ቆዳ ፡ ብርድ ፡ የማያስገባ ፡ በመሆኑ ፡ አንድ ፡ ዕዳ ፡ ወርዶላቸዋል ፤ ለልብስ ፡ አያስቡምና ። ሰው ፡ ግን ፡ አካሉ ፡ ከብርድ ፡ የሚጠበቅበት ፡ ጠጉር ፡ ስለሌለው ፡ ለልብሱ ፡ ማሰብ ፡ አለበት ።

ስለዚህ ፡ የጥንት ፡ ሰዎች ፡ የልብስ ፡ ዘዴ ፡ ተገኝቶ ፡ ሰውነታቸውን ፡ እስኪሸፍኑ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ተቸግረው ፡ ኖረዋል ። የመጀመሪያ ፡ ልብሳቸውም ፡ ቅጠልና ፡ ያውሬ ፡ ቆዳ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ አራዊት ፡ እንዳይበሏቸው ፡ ይፈራሉ ፤ ደካማ ፡ ናቸውና ፡ በታመሙም ፡ ጊዜ ፡ ለመታከም ፡ ዕውቀት ፡ ስላልነበራቸው ፡ በሽታ ፡ ሲይዛቸው ፤ ወይም ፡ ሲቈስሉ ፡ ሥቃያቸው ፡ ይበዛ ፡ ነበር ።

አውሬ ፡ አድነው ፡ ለመመገብ ፤ ዕንጨት ፡ ለመቈረጥ ፤ ሰው ፡ የሚጣላ ፡ አውሬ ፡ በመጣባቸው ፡ ጊዜም ፡ ለመከላከል ፡ የሚችሉበት ፡ መሣሪያ ፡ አልነበራቸውም ። መጀመሪያ ፡ መሣሪያ ፡ የሠሩት ፡ ድንጋይ ፡ እየጠረቡ ፡ ነው ። ቋንቋ ፡ እስኪፈጠር ፡ ድረስም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚናገሩት ፡ በድምፅና ፡ በምልክት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን፡ አልቀረም ። ቤት ፡ ለመሥራት ፡ ዕውቀት ፡ እስኪያገኙ ፡ ድረስ ፡ የሚኖሩትም ፡ በየዋሻው ፡ ውስጥ ፡ ነበር ።



የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ ይኖሩ ፡ እንደነበር ፡ ባሁን ፡ ዘመን ፡ ያሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ለማወቅ ፡ አስበው ፡ ይኖሩበት ፡ የነበረውን ፡ ዋሻ ፡ ሲመረምሩ ፡ በአጥንት ፤ በዝሆን ፡ ጥርስ ፤ በቀንድ ፡ ስባሪ ፡ ላይ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አውሬ ፡ ስዕል ፡ ተስሎ ፡ እያገኙ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ይደነቃሉ ። የሚደነቁበትም ፡ ምክንያት ፡ በዚያን ፡ በድንቁርና ፡ ዘመን ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ፍቅር ፡ ተሰምቷቸው ፡ ስዕል ፡ ለመሳል ፡ በማሰባቸው ፡ ነው ። ስለውነት ፡ በተገኘውም ፡ ስዕል ፡ ላይ ፡ የዱሩ ፡ የፈረስ ፤ የዝሆን ፤ የበሬ ፤ የሌላም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አውሬና ፡ እንስሳ ፡ መልክ ፡ ይታያል ።

የጽሕፈት ፡ ዘዴ ፡ የተገኘው ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ መንገድ ፡ ነው ። ከጥንት ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ የጽሕፈትን ፡ ዘዴ ፡ በስዕል ፡ መንገድ ፡ አግኝተው ፡ የሠሩበት ፡ ግብፆች ፡ ስለሆኑ ፡ የጽሕፈት ፡ ጥበብ ፡ በእነሱ ፡ ነው ፡ የተገኘው ፡ እየተባለ ፡ ዛሬ ፡ ይታሰባል ። ምክንያቱም ፡ «ሂየሮግሊፍ ፡» የተባለው ፡ የእነሱ ፡ የጥንት ፡ ፊደል ፡ በሰጽዋት ፡ በእንስሳትና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃ ፡ እየተሳለ ፡ ስለሚገለጥ ፡ ነው ። የዚህ ፡ አጻጻፍ ፡ ምሥጢር ፡ በሊቃውንት ፡ መርማሪነት ፡ ታውቆ ፡ ፍቺው ፡ ተገኝቶ ፡ ለማንበብ ፡ እስኪቻል ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ አስፈልጎታል ።

ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ለኑሮው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ለማግኘትና ፡ ለመሥራት ፡ እስኪችል ፡ ድረስ ፡ በዕውቀቱና ፡ በጉልበቱ ፡ ብዙ ፡ እንደደከመ ፡ አይጠረጠርም ። ምግቡን ፡ የሚያበስልበት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ለመሥራት ፡ እስኪችል ፡ ድረስ ፡ እንኳ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ፈጅቶበታል ። ሰው ፡ በዚህ ፡ አካሄድ ፡ ያደረገውን ፡ እርምጃ ፡ መከታተልና ፡ መመርመር ፡ ልዩ ፡ ዕውቀትና ፡ ልዩ ፡ ትጋት ፡ የሚያስፈልገው ፡ ለብቻው ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ጥበብ ፡ ስለሆነ ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ይህንኑ ፡ እየተከታተሉና ፡ እየመረመሩ ፡ በየጊዜው ፡ ብዙ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ይገልጣሉ ።

አንዳንዶችም ፡ ታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ ሲናገሩ ፤ ከታሪክ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ይኖሩበት ፡ በነበረው ፡ ቦታ ፤ በመቃብራቸው ፤ በቤት ፡ ዕቃቸው ፤ ዓሣ ፡ በሚያጠምዱበትና ፡ አውሬ ፡ በሚያድኑበት ፡ መሣሪያቸው ፡ በኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሥራቸው ፤ የተገኘውን ፡

ማስረጃ ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ ዕውቀታቸውን ፡ ስንገምተው ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ ብልሆች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ እንረዳዋለን ። የብልህነታቸውም ፡ ደረጃ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለማናገር ፡ ገና ፡ አልተቻለም ፡ ይላሉ ።

የሰው ፡ ዘር ፡ ካዳምና ፡ ከሔዋን ፡ ወጥቶ ፡ እየተባዛና ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ እየተበታተነ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቦች ፡ በየበኩላቸው ፡ መንግሥት ፡ መሠረቱ ። የሰዎች ፡ ታሪክም ፡ በትክክል ፡ ለመታወቅ ፡ የተቻለው ፡ መንግሥት ፡ ከመሠረቱና ፡ የሠሩትንም ፡ ሥራ ፡ በጽሕፈት ፤ በሐውልት ፤ በኪነ ፡ ጥበብ ፡ እየገለጡ ፡ ለትውልድ ፡ ማስተላለፍ ፡ ከቻሉ ፡ በኋላ ፡ ነው ። እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ የነበረው ፡ ግን ፡ ጨለማ ፡ የሸፈነው ፡ ስለሆነ ፡ የተረጋገጠ ፡ ታሪክ ፡ አይደለምና ፡ ከታሪክ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ዘመን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ሰው ፡ ራቁቱን ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ የሚበላውንና ፡ የሚጠጣውን ፡ የሚለብሰውንም ፡ ሠርቶ ፡ በማግኘት ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ አሳቡ ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ከመመኘት ፡ አለማቋረጡና ፡ ረቂቅ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ሁልጊዜ ፡ ሲፈልግ ፡ መታየቱ ፡ በተፈጥሮው ፡ መሠረቱ ፡ የተከበረ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳናል ። አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሊቅ ፡ ሲናገር ፡ «ሰው ፡ የተሰደደ ፤ የተጋዘ ፤ አምላክ ፡ ነው ፡ » አለ ። አምላክ ፡ ሲል ፡ ሥን ፡ ፍጥረቱ ፡ ከሌሎች ፡ ፍጡሮች ፡ የበለጠ ፡ በታላቅነቱም ፡ ያምላክ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ለማለት ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ በአምሳላችን ፡ ሰውን ፡ እንፍጠር ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ ሲሠራ ፡ ጭቃ ፡ አድበልብሎ ፡ ካበጀ ፡ በኋላ ፡ እፍ ፡ ብሎበት ፡ ነፍስ ፡ ሰጠው ፡ ሲል ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይናገራል ። እንግዲህ ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ትንፋሽ ፡ የወጣና ፡ በሱ ፡ አምሳል ፡ የተሠራ ፡ በመሆኑ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ በሚያገኘው ፡ ነገር ፡ አሳቡ ፡ ጠግቦ ፡ አያውቅም ።



## የመንግሥታት ፡ መቋቋም ።

እንግዲህ ፡ ከውኃ ፡ ጥፋት ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ሰዎች ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ተበታትነው ፡ በየበኩላቸው ፡ መንግሥት ፡ የመሠረቱት ። ከሁሉም ፡ አገር ፡ አስቀድሞ ፡ ኑሮን ፡ በማሻሻል ፡ በሥልጣኔ ፡ ረገድ ፡ ቀደምትነቷ ፡ የታወቀ ፡ ግብፅ ፡ ነች ። ነገሥታቶቿ ፡ የፒራሚድን ፡ ሐውልቶች ፡ ሠርተው ፡ ይኸው ፡ ብዙ ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ ኖረው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ሳይፈርሱ ፡ ቆመው ፡ ይታያሉ ።

የግብጽ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በእርሻና ፡ የመቅደስ ፡ ሕንፃ በመሥራት ፡ ሕዝብን ፡ በመልካም ፡ ሕግ ፡ በማስተዳደር ፡ ቀደምትነት ፡ ነበራቸው ። የቀን ፡ መቁጠሪያም ፡ ደንብ ፡ ነበራቸው ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ የሥዕል ፡ ፊደል ፡ አውጥተው ፡ ታሪካቸውን ፡ በመጻፋቸው ፡ ይመሰገናሉ ።

ከግብፆች ፡ በኋላ ፡ የሠለጠኑ ፡ በሜዞጶታሚያ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ የአሦርና ፡ የባቢሎን ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ ግብፅንና ፡ እስራኤላውያንን ፡ ገዙ ። በአስትሮኖሚና ፡ (በከዋክብት ፡ ዕውቀት) ፡ በሒሣብ ፡ (ማቴማቲክ) ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ ነበራቸው ። ቀጥሎ ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ተነሥቶ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ ገዛቸው ።

በሶርያ ፡ አገር ፡ በሜዲቴራኔ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ ፊንቄ ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ በመርከብ ፡ እየዞሩ የሚነግዱ ፡ ሕዝቦች ፡ ነበሩ ። እነሱም ፡ የፊደልን ፡ ጥበብ ፡ አውጥተው ፡ ሠሩበት ። በኋላም ፡ ለግሪኮች ፡ አውርሰው ፡ ግሪኮችም ፡ ለሮማውያን ፡ ሮማውያንም ፡ ለአውሮፓ ፡ አስተላልፈው ፡ ይኸው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በእነሱ ፡ ፊደሎች ፡ አውሮፓውያን ፡ ይጽፉበታል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ፊደሎች ፡ ከንዱ ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ ሕዝብ ፡ በተላለፉ ፡ ቁጥር ፡ ተቀባዩ ፡ እያረመ ፡ ያሁኑን ፡ መልክ ፡ እስኪይዙ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተሻሽለዋል ። ቀጥሎ ፡ የግብፅም ፡ የሜዞጶታሚያም ፡ ሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ግሪኮች ፡ ተላለፈች ። ግሪኮች ፡ ግን ፡ ጥበብን ፡ በየቅርንጫፉ ፡ እያስፋፉ ፡ ስለሄዱ ፡ ሥጣኔን ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ደረጃ ፡ አደረሷት ።

ወደፊት ፡ እንደምንመለከተው ፡ ጦርነት ፡ ሥልጣኔ ፡ ሀብት ፡ እነዚህ ፡ ሶስት ፡ ነገሮች ፡ የሕዝብ ፡ ትልቅነትና ፡ ሕይወት ፡ የሚመሠረትባቸው ፡ መደቦች ፡ ናቸው ።

አንድ ፡ ሕዝብ ፡ በጀግንነት ፡ እየተከላከለ ፡ ነፃነቱን ፡ ጠብቆና ፡ ያገሩን ፡ ጠረፍ ፡ አስከብሮ ፡ ይኖራል ። ነገር ፡ ግን ፡ በሥልጣኔ ፡ የሚበልጠው ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ በተነሣበት ፡ ጊዜ ፡ የልብ ፡ ድፍረትና ፡ የጀግንነት ፡ ወኔ ፡ ከጥበብ ፡ ጋር ፡ ሊቋቋም ፡ ስለማይችል ፡ ይሸነፋል ። ይኸውም ፡ በግሪክና ፡ በፋርስ ፡ መካከል ፡ የሆነው ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል ።

እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ሀብት ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ጀግንነት ፡ ከሌለው ፡ ኃይለኛ ፡ ሕዝብ ፡ በመጣበት ፡ ጊዜ ፡ ገንዘቡንም ፡ ቀምቶ ፡ እሱንም ፡ ባርያ ፡ ያደርገዋል ። ሀብት ፡ ከሌለው ፡ ደግሞ ፡ ሥልጣኔውን ፡ ለማስፋፋትና ፡ ኃይሉን ፡ ለማጠንከር ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ እነዚህ ፡ ሦስት ፡ ጌጋዎች ፡ ላንድ ፡ መንግሥት ፡ መሠረቱ ፡ ናቸው ። በእነዚህም ፡ በሦስት ፡ ምክንያቶች ፡ ሕዝቦች ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ እያሉ ፡ ገዢና ፡ ተገዢ ፡ እየሆኑ ፡ ይኖራሉ ።

በጦርነት ፡ ድል ፡ የሆነ ፡ ሕዝብ ፡ የባርነት ፡ ቀንበር ፡ ይወድቅበት ፡ ነበር ፡ ሲባል ፡ ባርነት ፡ ማለት ፡ ምንድነው ። ?



## የባርነት ፡ ትርጉም ፡

ሰው ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ በአርአያ ፡ ሥላሴ ፡ የተፈጠረውን ፡ ወንድሙን ፡ ባርያ ፡ አድርጎ ፡ መግዛት ፡ እንዴት ፡ ደግሞስ ፡ መቼ ፡ እንደጀመረ ፡ ታሪክ ፡ ምንጩን ፡ አይነግረንም ። በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ፡ ብቻ ፡ ኖኅ ፡ ለወንድሞችህ ፡ ተገዛ ፡ ብሎ ፡ ልጁን ፡ ካምን ፡ እንደረገመውና ፡ አብርሃምም ፡ አጋር ፡ የምትባል ፡ ባርያ ፡ እንደነበረችው እናውቃለን ። ነገር ፡ ግን ፡ የኖኅ ፡ እርግማን ፡ በካም ፡ ዘር ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ መቼ ፡ በምንስ ፡ አኳኋን ፡ እንደሆነ ፡ አናውቅም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ዝርዝር ፡ ነገር ፡ ትተን ፡ በጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ ታሪክ ፡ ስንመለከት ፡ በጣም ፡ ከራቀው ፡ ከጥንት ፡ ዘመን ፡ ሕዝቦች ፡ አንስቶ ፡ ባርነት ፡ እንደነበረ ፡ እንረዳዋለን ። በግብፆች ፡ በእስራኤላውያን ፡ በግሪኮች ፡ በሮማውያን ፡ በሌሎችም ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ባሮች ፡ ነበሩ ። የባርነት ፡ ቀንበር ፡ የሚወድቅባቸውም ፡ ሰዎች ፡ ባልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ ነው ።

ባርነት ፡ የሚመጣባቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ።

ከዘር ፡ ማለት ፡ ከባርያ ፡ በመወለድ ።
አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ለገንዘብ ፡ ሲሉ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ይሸጣሉ ።
አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ችግር ፡ ሲበዛባቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ይሸጣሉ ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ገንዘብ ፡ ተበድሮ ፡ መክፈል ፡ ያልቻለ ፡ ለአበዳሪው ፡ ባርያ ፡ ሆኖ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ።
በጦርነት ፡ ላይ ፡ ማረኪው ፡ ተማረኪውን ፡ ለሕይወቱ ፡ ምሕረት ፡ ሲያደርግለት ፡ ባርያ ፡ ያደርገዋል ።

ሰው ፡ እያፈኑ ፡ ባርያ ፡ በሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ ማለት ፡ በባርያ ፡ ፈንጋዮች ፡ እጅ ፡ የወደቀ ፡ ባርያ ፡ ሆኖ ፡ መሸጥና ፡ መለወጥ ፡ ይደርስበታል ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ባሮች ፡ የሚሆኑ ፡ በጦርነት ፡ የተሸነፉ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ። ብዙ ፡

የባርያ ፡ ነጋዴዎች ፡ ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ቦታ ፡ አብረው ፡ እየሄዱ ፡ የጦር ፡ ምርኮኞችን ፡ ከድል ፡ አድራጊዎች ፡ ላይ ፡ በጅምላ ፡ እየገዙ ፡ ወስደው ፡ በየአገሩ ፡ በዝርዝር ፡ ይሸጡዋቸው ፡ ነበር ። በብዙም ፡ አገሮች ፡ ባሮቹ ፡ እየተዋለዱ ፡ ሲበዙ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቍጥራቸው ፡ ከቀረው ፡ ሕዝብ ፡ የበለጠ ፡ ሆኗል ። የባርነት ፡ ቀንበር ፡ የወደቀባቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁልጊዜ ፡ ከባድ ፡ ሆኖባቸዋል ።

ሠርተው ፡ በድካማቸው ፡ ያፈሩትን ፡ ወይም ፡ በውርስ ፡ ያገኙትን ፡ ወይም ፡ በስጦታ ፡ የተቀበሉትን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ የሚሰጡት ፡ ለጌታቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባሮች ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ በምንም ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ባለቤትነት ፡ ሊኖራቸው ፡ ዘንድ ፡ አይፈቀድላቸውም ። እስከ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድረስም ፡ ጌታ ፡ ባርያውን ፡ ለመግደል ፡ ሥልጣን ፡ ነበረው ። በጠቅላላው ፡ በሕዝብ ፡ መተዳደሪያ ፡ ሕግ ፡ ፊት ፡ ባሮች ፡ እንዳልተፈጠሩ ፡ ያህል ፡ ሆነው ፡ ነበር ፡ የሚታዩት ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ይህን ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ የተገዢነት ፡ ቀንበር ፡ ከጫንቃቸው ፡ ለማስወገድ ፡ ሲሉ ፡ ባሮች ፡ በሮማውያን ፡ ዘንድ ፡ አድማ ፡ አድርገው ፡ እየተነሡ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በብርቱ ፡ እንደተዋጉ ፡ በታሪክ ፡ እናገኛዋለን ። አንድ ፡ ጊዜማ ፡ ስፖርታኩስ ፡ በሚባል ፡ ሰው ፡ መሪነት ፡ ሰባ ፡ ሺ ፡ ባሮች ፡ ተነስተው ፡ ባደረጉት ፡ ውጊያ ፡ ሮማን ፡ ሊያጠፉዋት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልቀራቸውም ፡ ነበር ።

ነፃነት ፡ ካገኙም ፡ በኋላ ፡ ከጨዋዎች ፡ ልጆች ፡ እኩል ፡ ይቆጠሩ ፡ ዘንድ ፡ መብት ፡ ስላልተሰጣቸው ፡ የሚጠሩት ፡ በጌታቸው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ በእሱ ፡ ውስጥ ፡ እየሠሩ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ አልነበራቸውም ። በመንግሥት ፡ ውስጥም ፡ ማዕርግ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ለመሥራትና ፡ ከጨዋዎች ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ለመጋባት ፡ አልተፈቀደላቸውም ።

እንግዲህ ፡ ባርያ ፡ ማለት ፡ የተናቀ ፡ የተዋረደ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ባሮች ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ከተሰጠው ፡ ከማናቸውም ፡ ደስታ ፡ እንዳይ



ካፈሉ ፡ የተከለከሉ ፡ ፍጡሮች ፡ ሆነው ፡ ኖረዋል ። በሕይወታቸው ፡ የሚደርስባቸውም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግፍና ፡ መከራ ፡ የጸና ፡ በመሆኑ ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ የተወለዱበትን ፡ ቀን ፡ ከመርገም ፡ አላቋረጡም ፤ ይህንኑም ፡ ወደፊት ፡ ታሪክ ፡ እያመሳከርን ፡ በምንመለከተው ፡ እናገኘዋለን ። በመሬት ፡ ኑሮ ፡ መከራ ስለጸናባቸው ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ባለቅኔ ፡

ለናንተ ፡ ሆናለች ፡ ፀሐይዋ ፡ ጨለማ ፤
የኃዘን ፡ ልቅሶ ፡ ነው ፡ የወፎቹም ፡ ዜማ ።
መራር ፡ ነው ፡ ለናንተ ፡ የማሩ ፡ ወለላ ፤
ደስታም ፡ የላችሁ ፡ ከመከራ ፡ ሌላ ።
እጣችሁ ፡ ሲወሰን ፡ በተራ ፡ እያለፈ ፤
ለጭንቅ ፡ ነውና ፡ ጥንቱን ፡ የተጻፈ ።

ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ስለባሮች ፡ እድል ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ፤ ይልቁንም ፡ በሮማውያንና ፡ በአሜሪካኖች ፡ ዘንድ ፡ ባሮች ፡ አሳራቸው ፡ የበዛ ፡ በመሆኑ ፡ የወደቀባቸውን ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ለማቅለል ፡ ሲሉ ፡ ራሳቸውን ፡ መግደል ፡ የሚጽናኑበት ፡ ልማድ ፡ አድርገው ፡ ነበር ።

ስመ ፡ ጥሩው ፡ ፈላስፋ ፡ አርስጣጣሊስ ፡ ሲናገር ፡ ባርያ ፡ ማለት ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ ዕቃ ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፤ ወይም ፡ ርስት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላል ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ ባርያ ፡ ማለት ፡ ሕያው ፡ የሆነ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ። መሣሪያ ፡ ደግሞ ፡ ሕያው ፡ ያልሆነ ፡ ባርያ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ በፍልስፍና ፡ አነጋገር ፡ ይገልጽልናል ። በማስተዋል ፡ ነገሩን ፡ ስንመለከተው ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዳምና ፡ ሔዋንን ፡ ከምድረ ፡ ገነት ፡ አስወጥቶ ፡ መሬት ፡ ስለናንተ ፡ የተረገመች ፡ ትሆናለች ፡ እሾክ ፡ አሜከላ ፡ ታበቅላለች ፡ ብሎ ፡ ረግሞ ፡ ላቡን ፡ ከግንባሩ ፡ ላይ ፡ ጠርጎ ፡ እንዲበላ ፡ አዳምን ፡ አዞታል ። እንግዴህ ፡ በርግማን ፡ የመጣ ፡ በመሆኑ ፡ ሥራ ፡ የተጠላ ፡

ነገር ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ሰው ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ መሥራትና ፡ መድከም ፡ ቢቀርለት ፡ ይወዳል ። ነገር ፡ ግን ፡ ካልሠሩ ፡ ለመኖር ፡ ስለማይችል ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሻሽልበት ፡ ዘዴ ፡ ፈለገ ። ወንድሙን ፡ ጨቁኖ ፡ በባርነት ፡ እያሠራ ፡ ከሥራው ፡ የተገኘውን ፡ ፍሬ ፡ ለራሱ ፡ በማድረግ ፡ ሳይሠራ ፡ ለመኖር ፡ የሚችልበትን ፡ ብልሀት ፡ አገኘ ።

ሰዎች ፡ አእምሮ ፡ አግኝተው ፡ የባርነትን ፡ ልማድ ፡ እስኪያስወግዱ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ አልፎዋል ። አእምሮ ፡ ለማግኘት ፡ የበቁትም ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖትና ፡ በሥልጣኔ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።



## እስራኤላውያን ።

ከሶርያ ፡ ደቡብ ፡ ከሜዴቴራኔና ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ መካከል ፡ በምትገኘው ፡ ፓሌስቲን ፡ በምትባለው ፡ አገር ፡ እስራኤላውያን ፡ የሚባሉ ፡ ሕዝቦች ፡ ነበሩ ። ታሪካቸው ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውሥጥ የሚገኘው ፡ ነው ። ትክክለኛ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት የተወደደ ፡ አብርሃም ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ነበር ። እግዚአብሔርም ፡ ዘርህን ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋና ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ክዋክብት ፡ ብዙ ፡ አደርገዋለሁ ፡ የትልቅ ፡ ሕዝብ ፡ አባት ፡ ትሆናለህ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገለት ። ዮሴፍ ፡ በወንድሞቹ ፡ ተሸጦ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ አገር ፡ ስለሄደ ፡ ረሀብ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አባቱ ፡ ያዕቆብ ፡ ከነልጆቹ ፡ ከግብፅ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ኖረ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ፈርዖኖች ፡ እስራኤላውያንን ፡ ባሮች ፡ አድርገው ፡ መንገድና ፡ ፒራሚድ ፡ ያሠሩዋቸው ፡ ጀመር ፡ ጨርሰው ፡ ሊያጠፉዋቸውም ፡ አሰቡ ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ አስነሥቶ ፡ ከፈርዖን ፡ ቀንበር ፡ አወጣቸው ።

አርባ ፡ ዓመት ፡ በበረሀ ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብቶላቸው ፡ ከነበረው ፡ ከከንዓን ፡ ምድር ፡ ደረሱ ። በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ የረዳቸው ፡ ቢባል ፡ እስራኤላውያን ፡ ካዳም ፡ ጀምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ የገለጠለትን ፡ እውነተኛውን ፡ ሃይማኖት ፡ ጠብቀው ፡ የኖሩ ፡ ሕዝቦች ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ አነጋግሮት ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ የአሥርቱ ፡ ቃላትን ፡ ሕግ ፡ ሰጣቸው ።

እውነተኛውን ፡ ንጹህ ፡ ሃይማኖት ፡ በመከተላቸው ፡ እስራኤላውያን ፡ ትልቅ ፡ ዋጋ ፡ እንደነበራቸው ፡ የምንረዳው ፡ ወደፊት ፡ እንደምናየው ፡ ከጥንት ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ በሥልጣኔ ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ የነበሩ ፡ ግሪኮችና ፡ ሮማውያን ፡ በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ በጣም ፡ የተሳሳቱ ፡ እንደነበሩ ፡ ስናስተያየው ፡ ነው ። ግብፆችማ ፡ የፈረንሣዩ ፡ ሊቅ ፡ በሱዩ ፡ እንደተናገረው ፡ «በግብፅ ፡ አገር ፡ ከሱ ፡ ከራሱ ፡ ከእውነተኛው ፡ አምላክ ፡ በቀር ፡ ሌላው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አምላክ ፡ ነበር ።" በፀሐይ ፡ በተኵላ ፡ በድመት ፡ በበሬ ፡ በዓዞ ፡ ያመልኩ ፡ ነበርና ።

እውነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ የምትገኝ ፡ በእስራኤላውያን ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቤ ፡ እያለ ፡ ሲጠራቸው ፡ ኖረ ። በበደሉትም ፡ ጊዜ ፡ አባት ፡ የሚወደውን ፡ ልጅ ፡ እንደሚቀጣ ፤ ይቀጣቸው ፡ ነበር ። ነገሥታቶቻቸውም ፡ ዳዊትና ፡ ሰሎሞን ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ነበሩ ። በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ የምትባልው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄዳ ፡ ከጥበበኛው ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ተዋውቃ ፡ ስትመለስ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ወለደች ። ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ደርሳ ፡ በመመለሷ ፡ ምኒልክን ፡ ብቻ ፡ አልነበረም ፡ ያተረፈችው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ የጻፈ ፡ አንድ ፡ የፈረንሣይ ፡ ደራሲ ፡ እንደተናገረው ፡ "በማህጸኗ ፡ ምኒልክን ፡ በልቧ ፡ የእውነተኛውን ፡ ሃይማኖት ፡ ዜና ፡ ይዛ ፡ ተመለሰች ።„ እንጂ ።

የሕዝቦችን ፡ ታሪክ ፡ ለማያያዝ ፡ እንዲመቸን ፡ ሆሜር ፡ የሚባለው ፡ የግሪኮች ፡ ትልቁ ፡ ባለቅኔ ፡ የነበረው ፡ ሰሎሞን ፡ በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ አቅራቢያ ፡ ነው ። ወደ ፡ እስራኤላውያን ፡ ታሪክ ፡ እንመለስና ፡ በኋላ ፡ ከልዳውያን ፡ የሚባሉ ፡ ሕዝቦች ፡ ድል ፡ አድርገዋቸው ፡ እስራኤላውያን ፡ በምርኮኛነት ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ሄዱ ። ኋላ ፡ ግን ፡ ቂሮስ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ባቢሎንን ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲመለሱ ፡ ፈቀደላቸው ። በመጨረሻም ፡ ከሮማውያን ፡ ቀንበር ፡ ውሥጥ ፡ ገብተው ፡ ሲኖሩ ፡ በአውግስጦስ ፡ ቄሣር ፡ ዘመን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ተወለደ ።



## ሆሜር ፡

ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ሆሜር ፡ የሚባለው ፡ የግሪክ ፡ ባለቅኔ ፡ « ኢሊያድ ፡ » እና ፡ «ኦዲሴ ፡ » የተባሉ ፡ ሁለት ፡ የቅኔ ፡ መጻሕፍት ፡ ጽፏል ። በማንኛውም ፡ ሕዝብና ፡ በማናቸውም ፡ አገር ፡ በማናቸውም ፡ ዘመን ፡ ከተነሡት ፡ ባለቅኔዎች ፡ ሁሉ ፡ ሆሜር ፡ ይበልጣል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የባለቅኔዎች ፡ መሥፍን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ቮልቴር ፡ ሲናገር ፡ «ድርሰት ፡ (ሊቴራቴር) የሌለው ፡ ሕዝብ ፡ ሕዝብ ፡ አይደለም ። » አለ ።

የጥንቲቱ ፡ ግሪክ ፡ ታላቅነት ፡ ዛሬ ፡ የለም ። ዓለም ፡ በድንቁርና ፡ ተከንኖ ፡ ሲኖር ፡ ብቻዋን ፡ በሥልጣኔ ፡ ጸድቃ ፡ ትኖር ፡ የነበረችው ፡ ግሪክ ፡ ውበቷን ፡ የሚመሠክሩ ፡ ሕንፃዎቿ ፡ ዛሬ ፡ ፈርሰዋል ፤ አርበኞቿም ፡ ረግፈዋል ፤ የሆሜር ፡ ቅኔ ፡ ግን ፡ እስከሁን ፡ ድረስ ፡ ቆይቶ ፡ ግሪክ ፡ ምን ፡ እንደነበረች ፡ ይገልጣል ፤ ያስተምራል ፤ ይናገራል ።

እርግጥ ፡ ነው ፡ የግሪክን ፡ ዝና ፡ ለማወቅ ፡ ከሆሜር ፡ ቅኔ ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የጻፉትን ፡ ማንበብ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የሆሜር ፡ ቅኔ ፡ ግሪኮች ፡ ጠባያቸው ፡ የታረመ ፤ ስሜታቸው ፡ የተራቀቀ ፤ አስተያየታቸው ፡ ጥበብ ፡ የሞላበት ፤ አሳባቸውም ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚመለከት ፡ መሆኑን ፡ ስለሚገልጥ ፡ ተነቦ ፡ አይጠገብም ። ሰው ፡ የሚያስደንቅ ፡ ጀግንነት ፡ ቢኖረው ፤ ታላላቅ ፡ ሕንፃዎች ፡ ቢያቆም ፤ አያሌ ፡ ሀብት ፡ ቢያከማች ፤ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ዕውቀት ፡ ቢመረምር ፤ ጠባዩ ፡ ክቡርነት ፤ አእምሮውም ፡ (ሞራል) መልካም ፡ አብነት ፡ ከሌለው ፡ የቀረው ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

በሆሜር ፡ ቅኔ ፡ ውስጥ ፡ ዋና ፡ ትምህርት ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው ፡ የጀግንነትና ፡ ያገር ፡ ፍቅር ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ዋናው ፡ ማኅደር ፡ ሲሆን ፡ በውስጡ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሳይጎድል ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ይገኝበታል ። ማናቸውም ፡ ሕዝብ ፤ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ስለግል ፡ ጠባዩ የሚያስፈልገውንና ፡ የሚወደውን ፡ ለሥልጣኔ ፡ የተስማማ ፡ የሆነውን ፡ ትምህርት ፡ ይቀዳበታል ።

ነገር ፡ ግን ፡ በሆሜር ፡ ቅኔ ፡ ውስጥ ፡ ለእኛ ፡ ላሁኖቹ ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ፡ ግራ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ ያማልክትና ፡ የሰዎች ፡ ሥራ ፡ ተቀላቅሎ ፡ ስለሚገኝበት ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እኛና ፡ ሆሜር ፡ ዘመናችን ፡ ልዩ ፡ መሆኑን ፡ አለመዘንጋት ፡ ይገባል ። እኛ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነን ፡ ሆሜር ፡ ግን ፡ አረመኔ ፡ ነበር ።

አረመኔ ፡ ስንል ፡ ባማርኛችን ፡ ትርጉሙ ፡ ሁለት ፡ ነው ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ጨካኝ ፡ ርኅራኄ ፡ የሌለው ፡ ማለት ፡ ይሆናል ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በእውነተኛው ፡ አምላክ ፡ ያላመነ ፤ ለጣዖት ፡ የሚያመልክ ፡ ማለት ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ሆሜር ፡ አረመኔ ፡ ነበር ፡ ስንል ፡ በመጀመሪያው ፡ ሳይሆን ፡ በሁለተኛው ፡ ትርጉም ፡ ነው ።

የጥንት ፡ ግሪኮች ፡ የሚያምኑት ፡ በብዙ ፡ አማልክት ፡ ነበር ። የእሳት ፡ አምላክ ፤ የጦርነት ፡ አምላክ ፤ የባሕር ፡ አምላክ ፤ እያሉ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ተግባርና ፡ ለያንዳንዱ ፡ ነገር ፡ አንዳንድ ፡ አምላክ ፡ ያደርጉለት ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ሴቶች ፡ አማልክት ፡ አሉ ። የጥበብ ፡ አምላክ ፡ ሴት ፡ ነች ፡ እሷም ፡ አቴና ፡ ትባላለች ። የውበት ፡ አምላክ ፡ አለች ፤ እሷም ፡ አፍሮዲት ፡ ትባላለች ። ወንዶቹም ፡ ሴቶቹም ፡ አማልክት ፡ ብዛታቸው ፡ ተቆጥሮ ፡ አያልቅም ። ወንዶች ፡ አማልክትም ፡ ሚስቶች ፡ አሉዋቸው ። ከሁሉም ፡ በላይ ፡ ጁፒቴር ፡ (ዜውስ)የሚባል ፡ አለ ። እሱም ፡ ያማልክት ፡ ሁሉ ፡ አምላክ ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛና ፡ በኃይሉ ፡ ሁሉንም ፡ የሚደመስስ ፡ ነው ። ያማልክት ፡ ሁሉ ፡ አባትና ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያምኑበታል ። ቲታኖችን ፡ ድል ፡ አደረገ ። አባቱን ፡ ሳቱርንን ፡ አሸንፎ ፡ ዙፋኑን ፡ ነጠቀው ። ለወንድሙ ፡ ለኔፕቱን ፡ ባሕርን ፡ ፕሉቶን ፡ ለሚባለው ፡ ላንደኛው ፡ ወንድሙ ፡ ደግሞ ፡ ገሃነምን ፡ ሰጥቶ ፡ የሲኦል ፡ ንጉሥና ፡ የሙታን ፡ አምላክ ፡ አደረገው ። እሱ ፡ ራሱ ፡ ጁፒቴር ፡ ግን ፡ ሰማይንና ፡ መሬትን ፡ ያዘ ፡ ይላሉ ። ያማልክቶቻቸው ፡ ታሪክ ፡ በሚቶሎጊ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

ሰው ፡ ደግ ፤ ወይም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ መልአክ ፡ ቀረበው ፡ ወይም ፡ ሰይጣን ፡ ተጠጋው ፡ እንደምንለው ፡ ሁሉ ፡ ግሪኮች ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ ጀግና ፡ ሲሆን ፡ ጁፒቴር ፡ ደገፈው ፤ አጽሎን ፡ ረዳው ፡ ተመልካች ፡ ሲሆንም ፡ የጥበብ ፡ አምላክ ፡ አቴና ፡ መከረችው ፡ ይላሉ ።



ጀግኖች ፡ የሆኑትንም ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ በአባታቸው ፤ ወይም ፡ በእናታቸው ፡ ካምላክ ፡ ይወለዳሉ ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበር ። በትሮይ ፡ ከተማ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ አማልክት ፡ ከሁለት ፡ ተከፍለው ፡ ግማሾቹ ፡ ከስፓርት ፡ ሰዎች ፡ ግማሾቹም ፡ ከትሮይ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ተዋግተዋል ። የሆሜር ፡ ቅኔ ፡ የሚናገረው ፡ በስፓርት ፡ ሰዎችና ፡ በትሮይ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ስለተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ነው ።

ታሪኩም ፡ እንዲህ ፡ ነው ። ፕሪያም ፡ የሚባል ፡ የትሮይ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ልጁ ፡ ፓሪስ ፡ ወይም ፡ አሌክሳንድር ፡ የሚባለው ፡ በእንግድነት ፡ ወደ ፡ ስፓርት ፡ ከተማ ፡ ሄደ ። የስፓርት ፡ ንጉሥ ፡ ሜኔላስ ፡ የሚባለው ፡ ፓሪስን አክብሮ ፡ ተቀብሎ ፡ አስተናገደው ። ፓሪስ ፡ ግን ፡ ውብ ፡ የነበረችውን ፡ የሜኔላስን ፡ ሚስት ፡ ሄሌን ፡ የምትባለውን ፡ አስኰብልሎ ፡ ወሰዳት ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሜኔላስ ፡ ይህን ፡ በደል ፡ ለመቀበል ፡ የትሮይን ፡ ከተማ ፡ ሊወጋ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ በመርከብ ፡ አስከትቶ ፡ ዘመተ ። የትሮይ ፡ ከተማ ፡ ተከባ ፡ ውጊያው ፡ አስር ፡ ዓመት ፡ ቆየ ። በመጨረሻ ፡ ትሮይ ፡ በዚሁ ፡ ውጊያ ፡ ጠፋች ፡ የጠፋችውም ፡ እስራኤላውያን ፡ ከግብፅ ፡ አገር ፡ በወጡ ፡ በ፲፻፰ ፡ ዓመታት ፡ የወሀ ፡ ጥፋት ፡ በሆነ ፡ በ፲፩፻ ፹፬ ፡ ዓመታት ፡ ነው ። የሆሜር ፡ ቅኔ ፡ የሚናገረው ፡ በዚህ ፡ ውጊያ ፡ ውስጥ ፡ የተሠራውን ፡ የጀግንነት ፡ ሥራና ፡ የሆነውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

እንግዴህ ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ ጣጣ ፡ ለብቻው ፡ አድርገን ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ መልካም ፡ ምሳሌና ፡ ትምህርት ፡ የሚሆነውንም ፡ ነገር ፡ ስንመለከት ፡ የሆሜር ፡ ቅኔ ፡ መሰል ፡ የሌለውና ፡ ውብ ፡ የሆነ ፡ ያንድ ፡ ዓለም ፡ ዜና ፡ የያዘ ፡ ሰፊ ፡ ታሪክ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።

ከሆሜር ፡ ቀጥሎ ፡ ሌሎች ፡ የግሪክ ፡ ባለቅኔዎች ፡ ነበሩ ። ኤሺል ፡ የሚባለው ፡ ዘጠና ፡ የቴአትር ፡ ድራማዎች ፡ ጽፏል ። ሶፎክል ፡ የሚባለውም ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ ሶስት ፡ ድራማዎች ፡ ጽፏል ። ኤሺል ፡ ራሱ ፡ ሲናገር ፡ «ታላቅና ፡ ሰፊ ፡ ድግስ ፡ በሆነው ፡ በሆሜር ፡ ቅኔ ፡ ዘንድ ፡ የኔ ፡ ቴአትር ፡ የጉሮሮ ፡ መክፈቻ ፡ ሆና ፡ የም

ትቀርብ ፡ ቃናሽ ፡ ምግብ ፡ ነች ፡ »ሲል ፡ በትህትና ፡ የሆሜርን ፡ ሥራ ፡ ክፍ ፡ የራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጐ ፡ መሰክሮዋል ።

ረናን ፡ የሚባለው ፡ የፈረንሣይ ፡ ሊቅ ፡ ሲናገር ፡ ከንድ ፡ ሺ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ወደፊት ፡ እውቀት ፡ እየሰፋ ፡ ሲሄድ ፡ አሁን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ተንቀው ፡ የሚያነባቸው ፡ ይጠፋል ፤ ሁለት ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ስለማ ይረክሱ ፡ መታተማቸውና ፡ መነበባቸው ፡ ይቀጥላል ። እነዚሁም ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ የሆሜር ፡ ቅኔ ፡ ናቸው ፡ አለ ።



## ትልቁ ፡ እስክንድር ።

የግሪክ ፡ አገር ፡ በብዙ ፡ ከተሞች ፡ የተከፋፈለች ፡ ሆና ፡ እያንዳንዱም ፡ ከተማ ፡ ልዩብቻው ፡ መንግሥት ፡ ነበረው ፡ ከነዚሁም ፡ ዋኖቹ ፡ አቴናና ፡ ስፓርት ፡ ነበሩ ። የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ በጣም ፡ የተፈራና ፡ የገነነ ፡ ስለነበር ፡ የግሪክን ፡ አገር ፡ ሊያስገብር ፡ አስቦ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወጋት ። ግሪክ ፡ ግን ፡ የሠለጠነች ፡ ስለነበረች ፡ የፋርስን ፡ ጦር ፡ ድል ፡ እያደረገች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መለሰችው ።

በአቴናና ፡ በእስፓርት ፡ መካከልም ፡ የመናናቅና ፡ የመቀናናት ፡ መንፈስ ፡ ስለነበረ ፡ ጣላት ፡ ከውጭ ፡ ሲመጣ ፡ አንድነት ፡ ተባብረው ፡ እየመከቱ ፡ የጋራ ፡ ጠላታቸውን ፡ ሲመልሱ ፡ ቆዩ ። የውጭ ፡ ጠላት ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ እየተዋጉ ፡ ስለተዳከሙ ፡ የመቄዶንያ ፡ መንግሥት ፡ በፊልጶስና ፡ በእስክንድር ፡ ዘመን ፡ ገዛቸው ።

ግሪክ ፡ እየደከመች ፡ በሄደችበት ፡ ጊዜ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ሕይወት ፡ ሰጥቷት ፡ ቆይታ ፡ ነበር ። እሱም ፡ ትልቅ ፡ ጦረኛ ፡ ስለነበረ ፡ ሶርያን ፡ ግብፅን ፡ ፋርስን ፤ በክትሪያን ፡ ይዞ ፡ እስከ ፡ ሕንድ ፡ አገር ፡ ድረስ ዘለቀ ። ከሱም ፡ በፊት ፡ ሕንድን ፡ የረገጠ ፡ አውሮፓዊ ፡ አልነበረም ።

ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ የግሪክን ፡ አገር ፡ አንድ ፡ አድርጐ ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ በፋርስ ፡ ላይ ፡ ሲዘምት ፡ ሰላሳ ፡ ሺህ ፡ ወታደሮችና ፡ አራት ፡ ሺህ አምስት ፡ መቶ ፡ ፈረሰኞች ፡ ብቻ ፡ ነበሩት ። የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ዳርዮስ ፡ ግን ፡ ከእስክንድር ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጋ ፡ በመጀመሪያ ፡ ስድስት መቶ ፡ ሺህ ፡ ወታደሮች ፤ በሁለተኛው ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ሁለት መቶ ፡ ሺህ ፡ ወታደሮች ፡ ነበሩት ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የግሪክ ፡ ጦር ፡ የሠለጠነ ፡ ስለነበር ፡ ዳርዮስ ፡ ሁለቱንም ፡ ጊዜ ፡ ተሸነፈ ፤ እስክንድርም ፡ በፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ።

በእስክንድር ፡ ምክንያት ፡ የንግድ ፡ ሥራና ፡ የመርከቦችም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ መዘዋወር ፡ ተስፋፋ ። የጥበብ ፡ (ሲያንስ) የቴክኒክ ፤ የኢንዱስትሪ ፡ እርምጃ ፡ ተፋጠነ ። ብዙ ፡ ያልታወቁ ፡ አገሮች ፡ ተከፈቱ ። የግሪክና ፡ የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ ተቀላቀሉ ። ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ የተነሣ ፡ የዓለም ፡ ታሪክ

ሁኔታ ፡ ተለወጠ ። ስለዚህ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፤ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከተነሡት ፡ ታላላቆች ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ሁኖ ፡ ይቆጠራል ።

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ አርስጣጣሊስን ፡ በመርዳቱ ፡ ለሥልጣኔ ፡ የሰጠውን ፡ ጥቅም ፡ ወደፊት ፡ እናገኘዋለን ። አስተምሮ ፡ ያሳደገው ፡ ይህ ፡ ትልቁ ፡ ሊቅና ፡ ፈላስፋ ፡ (አርስጣጣሊስ ፡ )ስለሆነ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ መንፈሱ ፡ በግሪክ ፡ ሥልጣኔ ፡ የታነፀ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ግዛቱን ፡ እያስፋፋ ፡ ሲሄድ ፡ አሳቡ ፡ ተገዢዎቹ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ሕዝቦች ፡ የግሪክን ፡ ቋንቋ ፡ እንዲማሩና ፡ ከተሞቻቸውን ፡ በግሪክ ፡ ፕላን ፡ እንዲሠሩ ፡ በማድረግ ፡ የግሪክን ፡ መንፈስና ፡ ሥልጣኔ ፡ ለዓለም ፡ ለማውረስ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አሳቡን ፡ በሰፊው ፡ ሲያዘጋጅ ፡ በባቢሎን ፡ ከተማ ፡ ሃሙራቢ ፡ በሚባለው ፡ ንጉሥ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ በድንገት ፡ ታሞ ፡ በሰላሳ ፡ ሶስት ፡ ዓመቱ ፡ አረፈ ። ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ወዲያው ፡ እንደሞተ ፡ የጦር ፡ አበጋዞቹ ፡ መንግሥቱን ፡ ተከፋፈሉት ።



## የ ግ ሪ ክ ፡ ፈ ላ ስ ፎ ች ።

ትልቁ ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ግሪክን ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ አድርጎ ፡ ሊገዛት ፡ አስቦ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ የስፓርትና ፡ የአቴን ፡ ከተሞች ፡ በመከከላቸው ፡ የነበረውን ፡ የመቀናናትና ፡ የመንቃቀፍ ፡ የመናናቅንም ፡ ቂም ፡ አስወግደው ፡ የጋራ ፡ ጠላታቸውን ፡ ለመከላከል ፡ ሲሉ ፡ ተስማሙ ። የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በእስያ ፡ ከሚገኙት ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ኃይለኛ ፡ ቢሆን ፡ ሥልጣኔው ፡ አሮጌ ፡ ነበር ። ግሪክ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ መንግሥቷ ፡ ጠባብ ፡ ሕዝቧም ፡ ቍጥሩ ፡ ያነሰ ፡ ቢሆን ፡ ሥልጣኔዋ ፡ አፍላነት ፡ ነበረው ።

በዚህ ፡ ስለጋራ ፡ ጉዳይ ፡ ባደረጉት ፡ ጦርነት ፡ ስፓርት ፡ እግረኛ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ስታቀርብ ፡ አቴና ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ ሰጠች ። ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ስፓርት ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሁከት ፡ ሲያገኛት ፡ አቴና ፡ ግን ፡ የጦር ፡ መርከቦቿን ፡ የንግድ ፡ መርከቦች ፡ አድርጋ ፡ ስለሠራችባቸው ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ በንግድ ፡ ከሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ ጥቅምና ፡ ሀብት ፡ ተካፋይ ፡ ሆነች ።

ስፓርት ፡ ሕዝቧ ፡ የሚኖሩት ፡ በርሻ ፡ ስለሆነ ፡ ከዓለም ፡ ተለያይተው ፡ ቀሩ ። መንፈሳቸውም ፡ አንቀላፋ ። የአቴና ፡ ከተማ ፡ ግን ፡ መርከቦች ፡ የሚወጡባትና ፡ የሚገቡባት ፡ ንግድም ፡ የሚከናወንባት ፡ ገበያ ፡ ስለሆነች ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሚኖሩ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕዝቦች ፡ ነጋዶች ፡ የሚመጡ ፡ ባህላቸውና ፡ ጠባያቸው ፤ ሃይማኖታቸውና ፡ መንፈሳቸው ፡ የተለያየ ፡ ከራቱ ፡ ማዕዘን ፡ የተጠራቀሙ ፡ ሰዎች ፡ ስለሚሰበሰቡባትና ፡ ስለሚገናኙባት ፡ አሳብን ፡ የምትቀሰቅስ ፡ መመርመርና ፡ ማስተዋል ፡ የምትሰጥ ፡ ከተማ ፡ ሆነች ።

ብዙ ፡ የተለዋወጠ ፡ አሳብ ፡ ያለበት ፡ ቦታ ፡ አንዱ ፡ አሳብ ፡ ከንደኛው ፡ እየተቃወሰ ፡ ስለሚፈርስ ፡ ሕጎችና ፡ ልማዶች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጥፋፋሉ ፡ ብዙ ፡ ሃይማኖቶች ፡ ባሉበት ፡ ሥፍራ ፡ ሰው ፡ ሁሉንም ፡ ንቆ ፡ በማንኛውም ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ የሌለው ፡ ተጠራጣሪ ፡ ከመሆን ፡ ይደርሳል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ መጀመሪያ ፡

ሃይማኖትን ፡ ነቃፊዎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ምናልባት ፡ ነጋዴዎች ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ። ብዙ ፡ አገር ፡ ከመዞርና ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ከመመርመር ፡ የተነሣ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ እየላላ ፡ ስለሄደ ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የሚገኘውን ፡ ትምህርት ፡ ሁሉ ፡ ከስህተትና ፡ ከመታለል ፡ ይቆጥሩታልና ። ሀብት ፡ እየበረከተ ፡ ሲሄድ ፡ ሕዝብ ፡ ለማሰብና ፡ ለመመራመር ፡ የሚችሉበት ፡ መልካም ፡ አኗኗርና ፡ ጸጥታ ፡ ሊያገኙ ፡ ቻሉ ። ንግድ ፡ በጣም ፡ እየበረከተ ፡ ሲሄድ ፡ የሒሣብ ፡ ትምህርት ፡ አብሮ ፡ ሠለጠነ ። የመርከበኞችም ፡ ሥራ ፡ ሲስፋፋ ፡ የከዋክብት ፡ ትምህርት ፡ (አስትሮኖሚ ፡ ) ትልቅ ፡ እርምጃ ፡ አደረገ ። ቀድሞ ከዋክብት ፡ የሚጠቅሙት ፡ ለመርከቦች ፡ መሪ ፡ በመሆን ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ አልፈው ፡ ተርፈው ፡ በፍጥረት ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ተሰውረው ፡ የሚኖሩትን ፡ ብዙዎች ፡ ነገሮች ፡ ምሥጢራቸውን ፡ በከዋክብት ፡ ውስጥ ፡ መርምረው ፡ ሊያገኙ ፡ ማሰብ ፡ ጀመሩ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ (አስትሮሎጂ ፡ ) የሚባል ፡ ጥበብ ፡ ተወለደ ። ከሰው ፡ ሃሳብ ፡ በላይ ፡ የሚገኙትን ፡ የማይመረመሩና ፡ የማይገለጡትን ፡ አያሌ ፡ ነገሮች ፡ ሰው ፡ በተፈጥሮ ፡ ጠባይ ፡ መንገድ ፡ እየተመራ ፡ ትርጉማቸውንና ፡ ምሥጢራቸውን ፡ ለማግኘት ፡ ስለደፈረ ፡ ጥበብ ፡ (ሲያንስ ፡ ) ተወለደችና ፡ የፍልስፍናም ፡ ትምህርት ፡ አብሮ ፡ ተጀመረ ።

ፍልስፍና ፡ መጀመሪያ ፡ የጀመረው ፡ በፊዚክ ፡ ነው ። ፍልስፍና ፡ በተወለደችበት ፡ በአቴና ፡ ከተማ ፡ ይህ ፡ የምናየውና ፡ የምንነካው ፡ ዓለም ፡ ምንጩና ፡ መሠረቱ ፡ ፍጻሜውስ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ መጣ ። «በእውነቱ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ አቶሞችና ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። » ሲል ፡ ዴሞክሪት ፡ የሚባለው ፡ ፈላስፋ ፡ መልስ ፡ ሰጠ ። እንግዴህ ፡ አቶም ፡ ጥንትም ፡ በግሪኮች ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ እንጂ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነው ።

በኋላ ፡ ግን ፡ ፍልስፍና ፡ በጣም ፡ የተስፋፋው ፡ እየዞሩ ፡ ጥበብን ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሶፊስቶች ፡ የተባሉ ፡ መምህራን ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። እነሱም ፡ ያልመረመሩትና ፡ ያልተከራከሩበት ፡ ፍልስፍናን ፡ የሚጠቅስ ፡ ጉዳይ ፡ አይገኝም ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ። ስለ ፡ ዓለም ፡



ጉዳይ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥያቄ ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ። ፖለቲካና ፡ ሃይማኖት ፡ የሚነካ ፡ ነገር ፡ እየተገኘባቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲከለከሉ ፡ አይሰሙም ፡ ነበር ።

እነሱም ፡ በፖለቲካ ፡ ረገድ ፡ በሁለት ፡ ክፍል ፡ ተከፈሉ ። አንዱ ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ሩሶ ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባይ መልካም ፡ ነው ። ሥልጣኔ ፡ ግን ፡ የክፋት ፡ ምንጭ ፡ ነው ። በተፈጥሮ ፡ ጠባይ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እኩል ፡ ናቸው ። ሰዎችን ፡ የበላይና ፡ የበታች ፡ ያደረጉዋቸው ፡ በሕዝብ ፡ መካከል የማዕርግ ፡ ደረጃን ፡ የመሠረቱ ፡ ሰው ፡ ሰራሽ ፡ የሆኑ ፡ ሕጎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ እያሉ ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር ።

ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ጀርመኑ ፡ ፈላስፋ ፡ እንደኒች ፡ ተፈጥሮ ፡ ጠባይ ፡ ከደግነትና ፡ ከክፋት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ነው ። በተፈጥሮ ፡ ጠባይ ፡ ረገድ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ። ሞራል ፡ (አእምሮ) ፡ የሚባለው ፡ ኃይለኞችን ፡ ለማገድና ፡ ለማስታገስ ፡ ደካሞች ፡ የፈጠሩት ፡ ነገር ፡ ነው ። ኃይለኛነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠባይና ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚጓጓለት ፡ ትልቁ ፡ ምኞት ፡ ነው ።( በኦቶክራሲ ፡ )ሥልጣን ፡ የሚመራ ፡ መንግሥት ፡ ከሌላው ፡ ሁሉ ፡ የተሻለና ፡ የተገባ ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ ወገን ፡ ነበር ።

ይህንንም ፡ አሳብ ፡ የሚደግፉ ፡ በአቴና ፡ የሚገኙ ፡ የሀብታሞች ፡ ወገኖች ፡ የሆኑ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ለመያዝ ፡ የሚፈልጉ ፡ ዴሞክራሲ ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ አታላይ ፡ አሳብ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ ጥቂቶች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የዴሞክራሲ ፡ መንግሥት ፡ በአቴና ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የተመረጠና ፡ የተወደደ ፡ ሆኖ ፡ በሚያስመሰግን ፡ አኳኋን ፡ ተቋቁሞ ፡ መኖሩ ፡ አልቀረም ። በስፓርትና ፡ በአቴና ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ በሚጠጋ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ጦርነት ፡ በተደረገበት ፡ ዘመን ፡ በአቴና ፡ ሥልጣኑን ፡ የያዙ ፡ የዴሞክራሲ ፡ ወገኖች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ መንግሥታችሁ ፡ ደካማ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ እየነቀፉ ፡ ሥልጣኑን ፡ እንዲለቁላቸው ፡ የሀብታሞች ፡ ወገኖች ፡ ከመዝለፍ ፡ አላቋረጡም ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ለእነዚህ ፡ ወገኖች ፡ መሪዎች ፡ ከሆኑት ፡ ብዙዎቹ ፡ ተጋዙ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ስፓርታ ፡ ድል ፡ ባደረገች ፡ ጊዜ ፡

መጀመሪያ ፡ በቀረበችው ፡ አሳብ ፡ ግዞተኞቹ ፡ ነፃ ፡ እንዲለቀቁ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ግዞተኞቹ ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ በጦርነቱ ፡ ዘመን ፡ ሥልጣኑን ፡ ይዘው ፡ በነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ተነሡባቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ያነሱት ፡ (ሬቮሊሲዮን ፡ ) አልያዘላቸውም ። በውጊያው ፡ ላይ ፡ መሪያቸው ፡ የነበረው ፡ ክሪዚያስ ፡ የሚባለው ፡ ተገደለ ። እሱም ፡ ከሠላሳዎቹ ፡ አባይ ፡ ገነኖች ፡ አንዱ ፡ የሚባለው ፡ ነው ።

ክሪዚያስ ፡ የሚባለውም ፡ የሰቅራጥስ ፡ ተማሪ ፡ የፕላቶን ፡ አጐት ፡ ነበር ። ሰቅራጥስ ፡ (ሶክራት ፡ ) የሚያስተምረው ፡ በቃሉ ፡ ብቻ ፡ ስለነበርና ፡ መጽሐፍም ፡ ስላልጻፈ ፡ ትምህርቱና ፡ ፍልስፍናው ፡ ለዓለም ፡ እንዲገለጽና ፡ ለትውልድ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ያደረጉ ፡ ፕላቶንና ፡ ክሴኖፎን ፡ ናቸው ። ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ እየተከተሉትና ፡ አብረውት ፡ እየዋሉ ፡ ጊዜያቸውን ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ በማሳለፍ ፡ ቃሉንም ፡ እየሰሙ ፡ ፍልስፍናን ፡ ይማሩ ፡ ነበር ። እነዚሁም ፡ ፕላቶንና ፡ አልሲቢያድን ፡ አንቲስቴኔንና ፡ አሪስቲፖን ፡ የመሰሉ ፡ ናቸው ።

በአሁኑ ፡ ዘመን ፡ ሕዝብ ፡ የሚታመስበትና ፡ የፖለቲካ ፡ ሰዎችም ፡ ፍጻሜ ፡ በሌለው ፡ ክርክር ፡ የሚጨቃጨቁበት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በእነሱም ፡ ዘመን ፡ ይነጋገሩበትና ፡ ይከራከሩበት ፡ ነበር ። እነሱም ፡ ከመምህራቸው ፡ ከሰቅራጥስ ፡ ጋር ፡ ሰው ፡ ባሳቡ ፡ ካልተመራመረ ፡ በቀር ፡ ሕይወት ፡ አለኝ ፡ ለማለት ፡ አይገባውም ፡ ብለው ፡ የሚያስቡ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ስለዚህ ፡ የማሰብ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተከፈተው ፡ በእነሱ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ምንጩና ፡ መሠረቱም ፡ እነሱ ፡ ናቸው ፡ ቢባል ፡ የተገባ ፡ ንግግር ፡ ነው ።

መምህራቸው ፡ ሰቅራጥስ ፡ ሥራ ፡ አይሠራም ፡ ነበር ፡ ለነገም ፡ ብሎ ፡ አያስብም ፡ ነበር ። ተማሪዎቹ ፡ ሲጋብዙት ፡ እየሄደ ፡ አብሮዋቸው ፡ ከቤታቸው ፡ ይበላል ። ተማሪዎቹም ፡ ይወዱት ፡ ነበር ፡ የሚወዱትም ፡ በጥበቡ ፡ ውስጥ ፡ ትህትና ፡ ስለነበረው ፡ ነው ። የጥበብ ፡ ወዳጅ ፡ እንጂ ፡ የጥበብ ፡ መምህር ፡ ሆኖ ፡ አይታይም ፡ ነበር ። «አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ አጥርቼ ፡ የማውቀው ፡ ይኸውም ፡ ምንም ፡ አለማወቄን ፡ መረዳቴ ፡ ነው ።» እያለ ፡ ይህን ፡ ለትምህርቱ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ መናገር ፡ ይወድ ፡ ነበር ።



ፍልስፍና ፡ የሚጀምረው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ስለሚያምንባቸው ፡ ነገሮች ፡ ስለሚያስተምራቸው ፡ ትምህርቶች ፡ ስለተረዳቸውና ፡ እውነቶች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ስለተቀበላቸው ፡ ዕውቀቶች ፡ መጠራጠርን ፡ በተማረ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ሰው ፡ ራሱ ፡ የሚያምናቸው ፡ እምነቶች ፡ በራሱ ፡ ዘንድ ፡ እርግጠኞች ፡ ሆነው ፡ ይቆጠራሉ ። የሚመኛቸውንም ፡ ነገሮች ፡ ያሳብ ፡ ቅርዕ ፡ ይሰጣቸዋል ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ የገዛ ፡ ራሱን ፡ መልሶ ፡ ካልመረመረ ፡ እውነተኛ ፡ ፍልስፍና ፡ አትገኝም ፡ በማለት ፡ ሰቅራጥስ ፡ ሲናገር ፡ አስቀድመህ ፡ «ራስህን ፡ እወቅ ፡» ይላል ።

እርግጥ ፡ ነው ፡ ከሱ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ጣሌስና ፡ እንደ ፡ ሄራክሊት ፡ ያሉ ፡ ብርቱ ፡ ሰዎች ፡ እንደነፓርሜኒዴ ፡ ያሉ ፡ ብልሆች ፡ እንደነፒታጎርና ፡ ኤምፔዶክል ፡ ያሉ ፡ ትንቢት ፡ የሚናገሩ ፡ ፈላስፎች ፡ ተነሥተዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ አብዛኞቹ ፡ እውቀታቸው ፡ በፊዚክ ፡ በኩል ፡ ነው ። ይህም ፡ ማለት ፡ ስለሚዳሰሰውና ፡ ስለሚሠፈረው ፡ ከሰው ፡ ውጭ ፡ ስላለው ፡ ዓለም ፡ ጉዳይ ፡ አዋጅ ፡ በመስጠትና ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቱን ፡ በመመርመር ፡ በኩል ፡ ነበር ። ሰቅራጥስ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከምትመረምሩዋቸው ፡ ዛፎችና ፡ ድንጋዮች ፡ ሌላውም ፡ ሁሉ ፡ ቀርቶ ፡ ከከዋክብቶች ፡ ይልቅ ፡ በፈላስፎች ፡ ዘንድ ፡ ይበልጥ ፡ የከበረ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። እሱም ፡ የሰው ፡ ናላ ፡ ነው ፡ ይል ፡ ነበር ። ሰው ፡ ምንድነው ? ምንስ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ? እነሆ ፡ የሰቅራጥስ ፡ ጥያቄዎች ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ። ይህን ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ መላ ፡ በመምታትና ፡ በመሠረታዊ ፡ ነገሮችም ፡ ላይ ፡ በመከራከር ፡ ሰቅራጥስ ፡ የሰውን ፡ ነፍስ ፡ ጠልቆ ፡ ሲመረምር ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ሥልጣኔን ፡ ላውሮፓ ፡ ያወረሱ ፡ የግሪክ ፡ ሊቃውንት ፡ ጥበብን ፡ መመርመር ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ጀመሩ ፡ ጥቂት ፡ ከተመለከትነው ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ባርነት ፡ ጉዳይ ፡ እንመለስ ። ግሪኮች ፡ በጣም ፡ የሠለጠኑና ፡ ብዙ ፡ መርከቦች ፡ የነበሩዋቸው ፡ ሀብታሞች ፡ ሆነው ፡ ሳሉ ፡ ባቴና ፡ ከተማ ፡ የሚኖሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ቁጥራቸው ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ሲሆኑ ፡ በእነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ የባሮቹ ፡ ቁጥር ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሺህ ፡ ይሆን ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ በፖለቲክም ፡ ሆነ ፡ በዜግኛነት ፡ ረገድ ፡ ምንም ፡ መብት ፡ አልነበረ-

ቸውም ። መብት ፡ የሌላቸው ፡ ሲባልም ፡ ምን ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ ትርጉሙን ፡ ወደፊት ፡ እናገኘዋለን ። "The Story of Philisophy" የተባለውን ፡ የዊል ፡ ዱራንትን ፡ ( መጽሐፍ ፡ ተመልከት ። )

የሶቅራጥስ ፡ ተማሪ ፡ ፕላቶን ፡ (አፍላጦን፡) ነው ። የፕላቶን ፡ ተማሪ ፡ ደግሞ ፡ አርስጣጣሊስ ፡ ነው ። ፕላቶን ፡ አእምሮ ፡ በሕዋሳት ፡ ላይ ፤ መንፈስም ፡ ምድራዊ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ የበላይነት ፡ ገለጠ ። በዓይን ፡ የማይታይ ፡ ሌላ ፡ ዓለም ፡ መኖሩንና ፡ ይኸውም ፡ የማይታይ ፡ ዓለም ፡ ለነፍሳችን ፡ እውነተኛው ፡ መኖሪያ ፡ አገርዋ ፡ መሆኑን ፤ ዘለዓለማዊ ፡ እውነት ፡ የምትገኝበትም ፡ አምላካዊው ፡ ዓለም ፡ ጥላና ፡ እድፍ ፡ የማይነካው ፡ ፍጹም ፡ ደስታም ፡ የሚገኝበት ፡ መሆኑን ፡ አስረድቶ ፡ ነፍሳችንም ፡ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ ከሚያቆራኙዋት ፡ ግንኙነቶች ፡ ተለያይታ ፡ ደስታን ፡ ከዘለዓለማዊ ፡ ሕይወት ፡ ጋር ፡ እንድታገኝ ፡ ልትሻ ፡ ያስፈልጋታል ፡ ሲል ፡ አስተማረ ። የፕላቶን ፡ ፍልስፍና ፡ «ከሰው ፡ መንፈስ ፡ የተገኘ ፡ የወንጌል ፡ መቅድም ፡ » ተብሎ ፡ ተሰየመ ። ፕላቶን ፡ ለክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ መንገድ ፡ ያዘጋጀ ፡ ፈላስፋ ፡ ነው ።

አርስጣጣሊስ ፡ ፍልስፍናን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ጥበብ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ በመልክ ፡ በመልኩ ፡ እየመረመረ ፡ አቅድ ፡ ሰጠው ። አርስጣጣሊስ ፡ የጻፋቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ወደ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ይጠጋሉ ። አንዳንዶቹም ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ይሆናሉ ፡ ይላሉ ። እነዚህም ፡ መጻሕፍት ፡ ስለፊዚክ ፤ ስለሰማይ ፤ ስለመስፋፋትና ፡ ስለመፍረስ ፤ ስለሜቴዎሮሎጊ ፤ ስለ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ባህሪ ፤ ስለእንስሳት ፡ ትውልድ ፡ ስለ ፡ ሬቶሪክ ፡ ስለ ፡ ቅኔ ፤ ስለፖለቲክ ፤ ስለ ፡ ሜታፊዚክና ፡ እነዚህንም ፡ ስለመሰሉት ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበባት ፡ የሚናገሩ ፡ ናቸው ።

በፊት ፡ የዓረቦች ፡ ሊቃውንት ፡ ኋላም ፡ አውሮፓውያን ፡ ከእነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ ለትውልድ ፡ ተላልፈው ፡ የደረሱትን ፡ እየተረጐሙ ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡ አግኝተውባቸዋል ። አርስጣጣሊስ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የቻለው ፡ ከሌሎቹ ፡ ፈላስፎች ፡ የበለጠ ፡ መልካም ፡ እድል ፡ በማግኘቱ ፡ ነው ። ስመ ፡ ጥሩውን ፡ ንጉሥ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድርን ፡ አስተምሮ ፡ ያሳደገ ፡ እሱ ፡ ነውና ። ብዙዎች ፡



የዓለም ፡ ሊቃውንትና ፡ ፈላስፎች ፡ አሳባቸውንና ፡ መርምረው ፡ በትምህርት ፡ የተረዱትንም ፡ ዕውቀት ፡ በሥራ ፡ ለመግለጥና ፡ ተረድቶ ፡ ለማስረዳት ፡ የሚችሉበት ፡ እድል ፡ አላገኙም ።

ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ግን ፡ መምህሩ ፡ አርስጣጣሊስ ፡ ጥበብን ፡ በማስረጃ ፡ እያጣራ ፡ እንዲገልጥ ፡ በግሪክ ፡ አገርና ፡ በእስያ ፡ ውስጥ ፡ የእንስሳትንና ፡ የዕጸዋትን ፡ ዘሮችና ፡ ዓይነቶች ፡ ከያገሩ ፡ እየሰበሰቡ ፡ የሚያቀርቡለት ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ የሚሆኑ ፡ ታዘው ፡ እንዲረዱትና ፡ እንዲያገለግሉት ፡ አድርጎለት ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ አዳኞች ፡ ደን ፡ ጠባቂዎች ፤ አታክልተኞች ፤ አሣ ፡ አጥማጆች ፡ ነበሩ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አርስጣጣሊስ ፡ በያይነቱ ፡ የእንስሳትና ፡ የዕጸዋት ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ የሚገኝበት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ታይቶ ፡ ያልታወቀ ፡ ትልቅ ፡ የዞኦሎጊክ ፡ አታክልት ፡ አቋቋመ ።

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ለሥራው ፡ ማከናወኛ ፡ የሚሆን በዛሬው ፡ ዘመን ፡ ሸረፋ ፡ ወደ ፡ አሥር ፡ ሚሊዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የሚጠጋ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥቶት ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ አርስጣጣሊስ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አያሌ ፡ መጻሕፍት ፡ ለመጻፍና ፡ ብዙ ፡ ጥበባትን ፡ ለመመርመር ፡ እንደቻለ ፡ ይህ ፡ ያስረዳናል ። እንግዲህ ፡ አርስጣጣሊስ ፡ ማለት ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ካወቅነው ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ሊቅ ፡ ስለባርነት ፡ ጉዳይ ፡ አሳቡን ፡ እንዲገልጥ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ባርያ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሊኖር ፡ የተገባ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያጸድቅ ፡ ነበር ። በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ማለቱ ? አርስጣጣሊስን ፡ የመሰለ ፡ ሊቅ ፡ ባርያ ፡ የመግዛትና ፡ የመሸጥ ፡ ልማድ ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ግፍ ፡ በአእምሮ ፡ በኩል ፡ አስቀያሚ ፡ መሆኑን ፡ አጥቶት ፡ ነውን ? መልሱን ፡ ወደፊት ፡ ስለምናገኘው ፡ አሁን ፡ የታሪክን ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ መከታተል ፡ እንመለስ ።

## ባሮች ፡ በግሪኮች ፡ ዘንድ ።

በግሪኮች ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ለሕይወቱና ፡ ለኑብረቱ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ እየሠሩ ፡ የሚያቀርቡና ፡ ሥራ ፡ የተባለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚያከናውኑ ፡ ባሮች ፡ ነበሩ ።

ዳቦ ፡ የሚጋግሩ ፤ ለከተማው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መብራት ፡ የሚሆነውን ፡ ጧፍ ፡ የሚያበጁ ፤ ወጥ ፡ የሚያስናዱ ፤ ልብስ ፡ የሚሰፉ ፤ የአናጢነት ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውኑ ፤ ወርቅና ፡ ብር ፡ እያነጠሩ ፡ ጌጥ ፡ የሚሠሩ ፤ ትምህርት ፡ የሚያስተምሩ ፤ የግብርናና ፡ የባላገር ፡ ሥራ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ የሚችሉ ፤ በመደብር ፡ ዕቃ ፡ የሚሸጡ ፤ የማዕድንና ፡ የእንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤ በጠቅላላው ፡ ማንኛውንም ፡ ሥራ ፡ የሚያደራጁ ፡ ባሮች ፡ ነበሩ ፡

ጌቶቻቸው ፡ ግን ፡ በየአደባባዩና ፡ በየገበያው ፡ እየተሰበሰቡ ፡ ስለ ፡ ፖለቲክ ፡ ጉዳይ ፡ ሲከራከሩ ፡ ይውላሉ ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ የኔ ፡ ኤሺል ፤ የኔ ፡ ሶፎክል ፤ የኔ ፡ ኧሪፒድ ፡ ቴአትር ፡ ወደሚታይበት ፡ ቦታ ፡ ይሄዳሉ ። ይህም ፡ ስለተባለ ፡ ግሪኮች ፡ ለባሮቻቸው ፡ እንደ ሮማውያን ፡ ጨካኞች ፡ አልነበሩም ። ሮማውያን ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ባሮቻቸውን ፡ ለአራዊት ፡ እየሰጡ ፡ የሚያስበሉበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።

ግሪኮች ፡ ግን ፡ ሕዝብ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ሊሠለጥን ፡ ስለማይችል ፡ ጨዎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ተዋርደው ፡ መሥራትን ፡ ስለማይፈቅዱና ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ የአንጎልና ፡ የመንፈስ ፡ ሥራ ፡ ስላለባቸው ፡ ባሮቻቸውን ፡ የሚገዟቸው ፡ በሥራ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጣጣ ፡ እንዲችሉላቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሮማውያን ፡ ሰዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ረስተው ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ አይቆጥሩዋቸውም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በመንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ባሮቻቸው ፡ በፖለቲካ ፡ ጉዳይ ፡ ድምፃቸውን ፡ ማሰማት ፡ አይፈቅድላቸውም ። ይህ ፡ ለጨዎች ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ መብት ፡ ነበር ።

የትሮይ ፡ ሰዎች ፡ የሜኔላስን ፡ ሚስት ፡ ሄሌንን ፡ እንዲመልሱልንና ፡ ነገሩ ፡ በእርቅ ፡ እንዲያልቅ ፡ ብንጠይቃቸው ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ኦዲሴውስ ፡ የሚባለው ፡ አስተዋይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ምክር ፡



አመጣ ። በዚህም ፡ የተነሣ ፡ ለንጉሡ ፡ ለሜኔላስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ነገረው ። «አንተ ፡ የስፓርት ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፤ አድምጠኝ ። ላንተ ፡ ለሄሌን ፡ ባል ፡ ተባብረን ፡ ልንከላከልልህ ፡ ቃል ፡ ገብተንልሃል ፤ ቃላችንንም ፡ እንፈጽማለን ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለጦርነት ፡ ታጥቀን ፡ ከመነሣታችን ፡ በፊት ፡ ሄሌንን ፡ በስምምነት ፡ መንገድ ፡ እንዲመልሱልን ፡ መሞከር ፡ አይገባንም ፡ ወይ ? ጦርነት ፡ ክፉ ፡ መዓት ፡ ነው ። ከተሞች ፡ ያቃጥላል ፡ መርከቦች ፡ ያጠፋል ፤ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ይፈጃል ፤ ቤት ፡ ሰቦችም ፡ ወጣቶችና ፡ ጐበዞች ፡ የሆኑ ፡ አርበኞቻቸው ፡ ሲሄዱ ፡ አይተዋቸው ፡ የሚመለስላቸው ፡ ግን ፡ መርዶ ፡ ነው ። ድል ፡ የሆኑት ፡ ሕዝቦችም ፡ ባሮች ፡ ይሆናሉ ። ሰዎችም ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ ሲሸጡዋቸውና ፡ ሲለውጧቸው ፡ ይኖራሉ ።»

ይህ ፡ ጥቅስ ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ዋናው ፡ የባርያ ፡ ምንጭ ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ ጦርነትም ፡ በሆነ ፡ ቁጥር ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ የሚፈሩት ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ከባርነት ፡ ቀንበር ፡ መግባትን ፡ እንደነበር ፡ ይገልጥልናል ።

ከሶቅራጥስ ፡ ተማሪዎች ፡ አንዱ ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ ፈላስፋ ፡ ፕላቶን ፡ (አፍላጦን ፡ ) «ወንድ ፡ ሆኜ ፡ እንጂ ፡ ሴት ፡ ሳልሆን ፡ ነፃ ፡ ሰው ፡ ሆኜ ፡ እንጂ ፡ ባርያ ፡ ሳልሆን ፤ ግሪክ ፡ ሆኜ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ያልሠለጠነ ፡ ሰው ፡ ሳልሆን ፤ በመወለዴ ፡ የፈጠረኝን ፡ አመሰግነዋለሁ ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ አምላኬን ፡ የማመሰግነው ፡ በሶቅራጥስ ፡ ዘመን ፡ ስለፈጠረኝ ፡ ነው ። » ብሎ ፡ ስለ ፡ ዕድሉ ፡ የተናገረውን ፡ የማይረሳ ፡ ቃል ፡ ተጽፎ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እናገኘዋለን ።

ነገር ፡ ግን ፡ ፕላቶን ፡ በዚያ ፡ ሁሉ ፡ እውቀቱ ፡ ባርያ ፡ ባለመሆኑ ፡ እየተመካ ፡ በተናገረው ፡ ቃል ፡ ተሳሳተ ። በነፃነቱ ፡ እንዳለ ፡ ሕይወቱን ፡ ሳይፈጅ ፡ ባርያ ፡ ሆኖ ፡ ተሸጠ ፡ ከተማሪዎቹ ፡ አንዱ ፡ አኒሴሪስ ፡ የሚባለው ፡ የተሸጠበትን ፡ ዋጋ ፡ ለገዛው ፡ ሰው ፡ ከፍሎ ፡ ነፃ ፡ አውጥቶታልና ። ፕላቶንን ፡ የመሰለ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ከባርነት ፡ በማውጣት ፡ የሚገኘውን ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ የደስታ ፡ ክብር ፡ ለማሻማት ፡ ሲሉ ፡ የፕ

ላቶን ፡ ወዳጆች ፡ ከሆኑት ፡ ከአቴና ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ብዙዎች ፡ የከፈልከውን ፡ ገንዘብ ፡ እናግባልህና ፡ ክብሩንና ፡ ደስታውን ፡ ለእኛ ፡ አሳልፍልን ፡ ሲሉ ፡ አኒሴሪስን ፡ ለምነውት ፡ ነበር ። አኒሴሪስ ፡ ግን ፡ ፕላቶንን ፡ ከባርነት ፡ በማውጣቴ ፡ ያገኘሁትን ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ለገንዘብ ፡ ተበልጬ ፡ አሳልፌ ፡ የምሰጥ ፡ ሰው ፡ አይደለሁም ፡ ሲል ፡ እምቢ ፡ አላቸው ።

የሰው ፡ ዕውቀት ፡ ዛሮ ፡ ዛሮ ፡ ጐደሎነት ፡ ስለማያጣ ፡ ፕላቶን ፡ ባርያ ፡ ባለመሆኑ ፡ በከንቱ ፡ ተመካ ። ጊዜ ፡ የሚያመጣውንና ፡ ዕድሜ ፡ የሚያቆየውን ፡ ነገር ፡ ዘልቆ ፡ ለማወቅ ፡ የሚችልበት ፡ ጥበብ ፡ ቢኖረው ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ አይናገርም ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፕላቶን ፡ በዚህ ፡ መሳሳቱ ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ይህንንም ፡ አሁን ፡ የጠቀስኩበት ፡ ምክንያት ፡ የፕላቶንን ፡ ስሕተት ፡ ለማሳሰብ ፡ ሳይሆን ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ በነፃነቱ ፡ በጣም ፡ ሊተማመንበት ፡ እንደማይችልና ፡ ከነፃነት ፡ ወደ ፡ ባርነት ፡ ለመውደቅም ፡ ቅርብ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለማስገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ነው ።



## ሮማውያን ።

ከእስክንድር ፡ በኋላ ፡ ሌሎች ፡ ኃያላን ፡ ሕዝቦች ፡ ተነሡ ። እነሱም ፡ ሮማውያን ፡ ናቸው ። ታሪካቸውም ፡ እንዲህ ፡ ነው ።

የትሮይ ፡ ከተማ ፡ ስትጠፋ ፡ የንጉሡ ፡ የፕሪያም ፡ ዘመድ ፡ የሆነ ፡ ኤኔ ፡ የሚባል ፡ መሥፍን ፡ ሸሽቶ ፡ ተሰደደ ። ከተማዋ ፡ ስትጠፋ ፡ ሸሽተው ፡ የተረፉትን ፡ ሰዎች ፡ አስከትሎ ፡ ካርር ፡ አገር ፡ ከተንከራተቱ ፡ በኋላ ፡ ዛሬ ፡ የሮማ ፡ ከተማ ፡ ከምትገኝበት ፡ አቅራቢያ ፡ ሰፍረው ፡ ከብዙ ፡ ትውልድ ፡ በኋላ ፡ ሮማ ፡ ተመሠረተች ። ከዚያም ፡ ኃይል ፡ እያገኙና ፡ ስማቸው ፡ እየገነነ ፡ ሔደ ።

ሮማውያን ፡ ከሌሎች ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ የተሻለ ፡ መልካም ፡ ሕግና ፡ የተመሠገነ ፡ አስተዳደር ፡ ነበራቸው ። ዋና ፡ ሙያቸው ፡ ጀግንነት ፡ ነበር ። በጦርነትም ፡ ላይ ፡ ሊመክትላቸው ፡ የሚችል ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ አልተገኘም ። ሁለት ፡ ዋና ፡ ጠባይ ፡ ነበራቸው ፡ ይኸውም ፡ ባለመልካም ፡ ምግባር ፡ መሆንና ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ነበር ።

የሚተዳደሩትም ፡ የሴና ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሚወስነው ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ሕግ ፡ ፈጻሚዎችና ፡ ነፃነታቸውንም ፡ ከማናቸውም ፡ ነገር ፡ ይልቅ ፡ አብልጠው ፡ የሚወዱ ፡ ነበሩ ።

ባጭሩ ፡ ሕዝብን ፡ ትልቅ ፡ የሚያደርግ ፡ ብዙ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ነበራቸው ። ራሳቸውንም ፡ ከሌሎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ አድርገው ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ዓለምን ፡ ለመግዛት ፡ አስበው ፡ ተነሡ ።

እውነትም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የታወቁትን ፡ በዙሪያቸው ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝቦች ድል አድርገው ፡ ገዟቸው ።

ቪርጊል ፡ የሚባለው ፡ የእነሱ ፡ ትልቁ ፡ ባለቅኔ ፡ ስለሮማውያን ፡ ሲናገር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

«እኔ ፡ በበኩሌ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ አብልጠው ፡ ሥራ ፡ መሥራትና ፡ ብረትንም ፡ በጥበብ ፡ ማንቀሳቀስ ፡ ያውቁበታል ።

ከእብነ ፡ በረድ ፡ ውስጥ ፡ ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ የሚመስሉ ፡ የሰው ፡ መልኮች ፡ እየቀረጹ ፡ ያወጣሉ ።

የሰማይን ፡ ክበብ ፡ በእርሳስ ፡ ይነድፋሉ ። የከዋክብትንም ፡ መነሣት ፡ ይናገራሉ ።

አንተ ፡ ሮማዊ ፡ የሆንክ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ሥራህ ፡ በግዛትህ ፡ ውስጥ ፡ ሕዝቦችን ፡ ማሰለፍ ፡ መሆኑን ፡ አትዘንጋ ። ያንተ ፡ ጥበብ ፡ የሰላምን ፡ ሕግ ፡ መስጠት ፤ የተገዙልህ ፡ ሕዝቦች ፡ ዕረፍትን ፡ እንዲያገኙ ፡ ማድረግና ፡ ኃያላንን ፡ ማስገበር ፡ ነው ።

ሮማውያን ፡ ሌላውን ፡ ሕዝብ ፡ የማስገበርን ፡ ሥራ ፡ ከቀረው ፡ ሙያ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ አድርገው ፡ ይመለከቱት ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ እነሆ ፡ ይህ ፡ ጥቅስ ፡ ያስረዳናል ። በዚህ ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ ዓለምን ፡ ሲገዙ ፡ ኖሩ ።

እስፓኝን ፤ ዛሬ ፡ ፈረንሣዊ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጐል ፡ የምትባለውን ፤ ግብፅን ፤ እንግሊዝን ፤ መቄዶንያን ፤ ግሪክን ፤ ትንሹ ፡ እስያን ፤ የሰሜን ፡ አፍሪካን ፡ ጠረፍ ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ አገሮች ፡ ከቀንበር ፡ ስር ፡ አገቧቸው ። ሮማውያን ፡ የግሪክን ፡ አገር ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ በያዙ ፡ ጊዜ ፡ ጥበብና ፡ ፍልስፍናን ፡ ከግሪኮች ፡ ላይ ፡ ዘርፈው ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ወሰዱ ። ግሪኮችም ፡ ለገዢዎቻቸው ፡ ለሮማውያን ፡ መምህራን ፡ ሆነው ፡ ሥልጣኔን ፡ ያስተምሩዋቸው ፡ ጀመር ።

ለምሳሌ ፡ ሲሴሮን ፡ የሚባለው ፡ የሮማ ፡ ሊቅ ፡ ትምህርቱን ፡ ሊያጠራ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ንግግርን ፡ የማሳመር ፡ ጥበብ ፡ (ኤሎክንስ) ሲማር ፡ በኖረበት ፡ ጊዜ ፡ ከንደበቱ ፡ የሚወጣውን ፡ ቃል ፡ በመስማት ፡ የትምህርት ፡ ጓደኞቹና ፡ መምህራኖቹ ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ እየተደነቁ ፡ ያመሠግኑት ፡ ነበር ።

ከግሪኮች ፡ መካከል ፡ አፖሎኒውስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሲሴሮን ፡ ሲናገር ፡ በሰማ ፡ ቁጥር ፡ እንደሌሎቹ ፡ በማመስገን ፡ ፈንታ ፡ አንገቱን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ አቀርቅሮ ፡ ይተክዝ ፡ ነበር ። ይህንኑ ፡ የሱን ፡ ሁኔታ ፡ ያስተዋለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደሚተክዝ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጠየቀው ።



«ምስኪኒቱ ፡ ግሪክ ፡ ከቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ የሚሰጣትን ፡ የበላይነቱን ፡ ደረጃ ፡ ይዛ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የኖረችበትን የንግግርን ፡ ጥበብ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ሊወስደው ፡ ሲዘርፈን ፡ እያየሁ ፡ ምነው ፡ አላዝን ፤ ምነው ፡ አልተክዝ» ብሎ ፡ አፖሎኒውስ ፡ መለሰለት ።

ሮማውያን ፡ ከግሪኮች ፡ ላይ ፡ ያልቀዱት ፡ ጥበብ ፡ የለም ። ቪርጊል ፡ የሚባለው ፡ ትልቁ ፡ ባለቅኔአቸው ፡ የሆሜርን ፡ አሳብ ፡ ተከትሎ ፡ «ኤኔኢዴ» ፡ የሚባለውን ፡ የሮማውያንን ፡ ጀግንነትና ፡ ትልቅነት ፡ የሚያመሰግንበትን ፡ ቅኔ ፡ ጻፈ ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ሮማውያን ፡ ዜውስን ፡ ጁፒቴር ፤ አቴንና ፡ ሚኔርቭ ፡ አፍሮዲትን ፡ ቬኑስ ፡ እያሉ ፡ በዲስ ፡ ስም ፡ እየጠሩ ፡ የግሪኮችን ፡ አማልክት ፡ ወስደው ፡ አመለኩባቸው ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ሮማውያን ፡ ከግሪኮች ፡ የተቀበሉትን ፡ ሥልጣኔ ፡ ለዓለም ፡ እንዲዳረስ ፡ አደረጉ ።

## ባሮች ፡ በሮማውያን ፡ ዘንድ ፤

ሮማውያን ፡ ከሜዲቴራኔ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ከተገዢነት ፡ ቀንበር ፡ ሲያገቧቸው ፡ የሚማርኳቸውን ፡ የጦር ፡ ምርኮኞች ፡ ባርያ ፡ እያደረጉ ፡ ይሸጧቸው ፡ ነበር ። ለተሸነፈ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ርኅራኄ ፡ አልነበራቸውም ።

ከርታጎን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ካጠፋዋት ፡ በኋላ ፡ ሴቶቹንና ፡ ሕፃናቶቹን ፡ ባርያ ፡ አድርገው ፡ ሸጡዋቸው ። የግሪክ ፤ የመቄዶንያ ፤ የእስፓኛ ፤ የሶርያ ፤ ሕዝቦች ፡ የሮማ ፡ ተገዥዎች ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ ሁከት ፡ ባነሡ ፡ ቍጥር ፡ ሮማውያን ፡ ሲወጓቸው ፡ ምርኮኞቹ ፡ የባርነት ፡ ቀንበር ፡ ወድቆባቸዋል ።

በሮማውያን ፡ ዘንድ ፡ ሴናተሮች ፤ ( የሴና ፡ አማካሪዎች ፡ ) ጄኔራሎችና ፡ ሀብታሞች ፡ ሰዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ የሚሠሩበት ፡ ርስትና ፡ ባርያ ፡ በመግዛት ፡ ነበር ። ድል ፡ አድርገው ፡ በሚይዙት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ርስት ፡ ገዝተው ፡ ባሮቻቸውን ፡ እያሠሩ ፡ ርስታቸውን ፡ ለማልማትና ፡ ሰብሉን ፡ እየሸጡ ፡ ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ይጣጣራሉ ። ለባሮቻቸውም ፡ ምንም ፡ ርኅራኄ ፡ ስላልነበራቸው ፡ ከድካም ፡ የተነሣ ፡ እየሞቱ ፡ ያልቁ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የሮማ ፡ ግዛት ፡ እየሰፋ ፡ የጦር ፡ ምርኮኞችም ፡ በባርነት ፡ የሚሸጡበት ፡ ገበያ ፡ እየበዛ ፡ ስለሄደ ፡ በሚሞቱት ፡ ባሮች ፡ እግር ፡ ሌሎች ፡ ባሮች ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ እየገዙ ፡ መተካት ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነበር ።

በሮማውያን ፡ ዘንድ ፡ ሕንፃዎች ፡ ሲሠሩ ፡ በማዕድንና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ በእርሻ ፡ ሥራ ፡ የሚፈለጉት ፡ ባሮች ፡ ነበሩ ።

በሮማ ፡ ባርያ ፡ የሚሸጠው ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በሐራጅ ፡ ነበር ። ከገበያ ፡ እያወጡ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ እንዲመለከታቸው ፡ ተብሎ ፡ ባሮቹን ፡ ከትልቅ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ያቆሟቸዋል ። ገዢዎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ባሮቹ ፡ በአካላታቸው ፡ ላይ ፡ ነውርና ፡



ጉድለት ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ አለባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ስለሚፈልጉ ፡ ለዚህ ፡ ተብሎ ፡ እየቀረቡ ፡ በግልጥ ፡ በዓይን ፡ ለማየት ፤ ወይም ፡ በእጅ ፡ ለመዳሰስ ፡ እንዲመቻቸው ፡ እርቃን ፡ ሥጋቸውን ፡ ነበር ፡ የሚያቆሟቸው ። በአንገታቸውም ፡ ላይ ፡ በማተብ ፡ የተንጠለጠለ ፡ ጠባያቸው ፡ በዝርዝር ፡ የተጻፈበት ፡ ትንሽ ፡ ሰሌዳ ፡ ታሥሮላቸው ፡ ገዢ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ያንን ፡ ካነበበ ፡ በኋላ ፡ የሚስማማውን ፡ ባርያ ፡ መርጦ ፡ ይገዛል ።

ከባሮቹም ፡ የሚፈለገው ፡ ዋና ፡ ዓይነተኛ ፡ ጠባይ ፡ ሙሉ ፡ ጤንነት ፡ ያለውና ፡ ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ ባርያ ፡ የሚጥል ፡ በሽታ ፡ የሌለበት ፡ የማይሰርቅ ፡ ራሱን ፡ ለመግደል ፡ የማያስብ ፡ የማይኮበልል ፡ እንዲሆን ፡ ነበር ። ባርያው ፡ ከተገዛበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ጠባዩ ፡ በሰሌዳው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ሳይሆን ፡ ቀርቶ ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ቢገኝበት ፡ የሸጠው ፡ ሰው ፡ መልሶ ፡ ይወስዳል ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ በጉዳቱ ፡ መጠን ፡ ባርያው ፡ ላጠፋው ፡ ጥፋት ፡ ካሣ ፡ ይከፍላል ። በሮማውያን ፡ ዘንድ ፡ በባላገር ፡ የእርሻ ፤ የአታክልት ፤ የከብት ፡ ማርባት ፡ ሥራ ፡ በከተማና ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ዳቦ ፡ የመጋገር ፡ ወጥ ፡ የመሥራትና ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ጥቃቅን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ባሮች ፡ ነበሩ ። አንድ ፡ መኳንንት ፡ ከሃያ ፡ እስከ ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ባሮች ፤ መካከለኛ ፡ ጌታ ፡ ሰው ፡ ከሁለት ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ባሮች ፡ ይገዛ ፡ ነበር ። አንድ ፡ መኰንን ፡ ወደ ፡ ግዛት ፡ ቦታ ፡ ሲሄድ ፡ በአውግሥጦስ ፡ ቄሣር ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ እስከ ፡ ሃያ ፡ ባሮች ፡ ድረስ ፡ ይዞ ፡ ለመሄድ ፡ ይፈቀድለት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በታሪክ ፡ ተጽፎ ፡ እናገኛለን ። ከባሮች ፡ መካከል ፡ ብዙዎቹ ፡ እንደናርሲስ ፡ በየጊዜው ፡ ለሮማ ፡ ቄሣሮች ፡ ባለሟሎች ፡ ለመሆን ፡ በቅተዋል ። አንዳንዶችም ፡ ደግሞ ፡ እንደነ ፡ ኤዞፕና ፡ እንደነ ፡ ፌድር ፡ ያሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ወጥቷቸዋል ። ሆራስ ፡ የሚባለው ፡ ትልቁ ፡ ባለቅኔ ፡ አባቱ ፡ ነፃ ፡ የወጣ ፡ ባሪያ ፡ ነው ። አናክሲላውስ ፡ የሚባለው ፡ የሬጂዮም ፡ ንጉሥ ፡ ሲሞት ፡ ሚሴት ፡ የሚባለውን ፡ ባርያውን ፡ ለልጆቹ ፡ ሞግዚት ፡ ለመንግሥቱ ፡ ጠባቂ ፡ አድርጎት ፡ ሞተ ። ሚሴትም ፡ ላገሩ ፡ ጥቅምና ፡ ለሕዝቡ ፡ ክብር ፡ የሚሆን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ መሥርቶ ፡ በሚያስመሰግን ፡ አኳኋን ፡ አገሩን ፡ ባስተዋይነት ፡ እያስተዳደረ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ያደራውን ፡ ሥራ ፡ ሲጨርስ ፡ ያለ ፡ ሁከት ፡ በሰላምና ፡ በታማኝነት ፡ መንግሥቱን ፡ ላልጋ ፡ ወራሹ ፡ አስረክቦ ፡ ሥልጣኑን ፡ ለቋል።

## የሮማ ፡ መውደቅ ፤

ሮማውያን ፡ ምንም ፡ ኃይለኞች ፡ ቢሆኑ ፡ ጀግንነታቸው ፡ ወሰን ፡ ነበረው ። ጀርመኖች ፡ ስላቮችና ፡ ታርታሮች ፡ አልተገዙላቸውም ፡ ነበርና ።

ስለዚህ ፡ ይልቁንም ፡ ከእስያ ፡ በኩል ፡ ታርታሮች ፡ የሚባሉት ፡ ሕዝቦች ፡ በየጊዜው ፡ እየተነሡ ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ እየወረረ ፡ ሲገፋው ፡ ይህ ፡ግፊያ ፡ ከጀርመኖች ፡ ላይ ፡ ደረሰ ። ጀርመኖች ፡ ደግሞ ፡ ድንበር ፡ አልፈው ፡ ሮማውያንን ፡ ሲገፉዋቸው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከሆነው ፡ መናወጥ ፡ የተነሣ ፡ የሮማ ፡ መንግሥት ፡ ተናጋ ። የተናጋውም ፡ መንግሥቱ ፡ በደከመበት ፡ ሰዓት ፡ ነው ።

ገኔራሎቻቸው ፡ መንግሥቱን ፡ በማስፋፋትና ፡ በማጽናት ፤ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ የመጣውን ፡ ጠላት ፡ በመመለስና ፡ በመደምሰስ ፡ አገልግለው ፡ ሥልጣን ፡ ሲጨብጡ ፡ በመቀናናትና ፡ በመታበይ ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ውጊያ ፡ እያበቀሉ ፡ ወገን ፡ በመለየታቸው ፡ የሬፑብሊኩን ፡ መንግሥት ፡ አፈረሱት ።

በማሪውስና ፡ በሲላ ፤ በጁሊዎስ ፡ ቄሣርና ፡ በፖምፔ ፤ በኦክታቭና ፡ በአንቷን ፡ መካከል ፡ የሆነው ፡ ጠብ ፡ የመንግሥቱን ፡ ኃይል ፡ እንደ ፤ ነቀዝ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ እያሰለሰለ ፡ የሕዝቡንም ፡ ጠባይ ፡ አበላሽቶት ፡ ነበር ።

እንደ ፡ ኔሮንና ፡ እንደ ፡ ካሊጉላ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በነገሡማ ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ የነበራቸው ፡ የትልቅነት ፡ ጠባይ ፡ ሁሉ ፡ ጨርሶ ፡ ጠፍቶ ፡ ለድሎትና ፡ ለጌጥ ፤ ለግልሙትናና ፡ ለጭካኔ ፡ ሥፍራ ፡ ለቆ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ በነበራቸው ፡ ጊዜ ፡ አኒባልን ፡ የመሰለ ፡ ብርቱ ፡ ጠላት ፡ እስከ ፡ ሮማ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ ሊያጠፋቸው ፡ ሳይችል ፤ ጠባያቸው ፡ በተበላሸ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በብዙ ፡ ጀግንነትና ፡ በረጅም ፡ ዘመን ፡ የተቋቋመውን ፡ መንግሥታቸውን ፡ ሌሎች ፡ ኃይለኞች ፡ ሕዝቦች ፡ መጥተው ፡ ሲያናውጡት ፡ እንደ ፡ አሮጌ ፡ ሕንፃ ፡ ተንዶ ፡ ወደቀ ።



የመንግሥቱን ፡ ጠረፍ ፡ ለመጠበቅ ፡ አቅም ፡ ባነሳቸው ፡ ጊዜ ፡ የምሥራቅና ፡ የምዕራብ ፡ መንግሥት ፡ ብለው ፡ መንግሥቱን ፡ ከሁለት ፡ ከፈሉት ።

በየጊዜው ፡ የመጡባቸውንም ፡ ወራሪዎች ፡ ሕዝቦች ፡ አገር ፡ እየሰጧቸው ፡ የሮማን ፡ መንግሥት ፡ እያገለገሉ ፡ እንዲኖሩ ፡ በስምምነት ፡ መንገድ ፡ ሊቀበሏቸው ፡ ሞክረው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ዘዴ ፡ ደካማነታቸውን ፡ ለጊዜው ፡ የሚያሻሽል ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ መንግሥቱን ፡ ሊያድነው ፡ አልቻለም ።

መጀመሪያ ፡ የጀርመን ፡ ሕዝቦች ፡ የምዕራቡን ፡ መንግሥት ፡ አጠፉት ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ቱርኮች ፡ የምሥራቁን ፡ መንግሥት ፡ አፈረሱት ።

ቪዚጎቶች ፡ የሚባሉ ፡ ከጀርመን ፡ ዘር ፡ የሆኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ተነሥተው ፡ አላሪክ ፡ በሚባለው ፡ ሰው ፡ መሪነት ፡ ሮማን ፡ ወረርዋት ። ሮማውያንም ፡ እንደ ፡ ተሸነፉ ፡ ሲረዱት ፡ ከተማቸውን ፡ እንዳይወርባቸው ፡ አላሪክን ፡ ለምነው ፡ የምትፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ እንሰጥሃለን ፡ አሉት ። እሱም ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ የወርቅ ፡ ገንዘብ ፤ ሠላሳ ፡ ሺህ ፡ የብር ፡ ገንዘብ ፤ አራት ፡ ሺህ ፡ የሐር ፡ ቀሚስ ፤ ሦስት ፡ ሺህ ፡ የግምጃ ፡ ጨርቅ ፡ ጣቃ ፤ አንድ ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ኪሎ ፡ የሚመዝን ፡ ቊንዶ ፡ በርበሬ ፤ ተቀብሎዋቸው ፡ ተመለሰ ።

ካንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ተመልሶ ፡ ሮማን ፡ ከበባት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ማናቸውንም ፡ ሀብት ፡ ቢሰጡት ፡ አልገላገልም ፡ ብሎ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ገብቶ ፡ ወታደሮቹ ፡ ከተማይቱን ፡ እንዲበዘብዟት ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ አቃጥሏት ፡ ሄደ ። ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ የቫንዳሎች ፡ ንጉሥ ፡ ጌንሴሪክ ፡ የሚባለው ፡ ከሮማ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ገብቶ ፡ ወታደሮቹ ፡ ከተማዋን ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ቀንና ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ሌሊት ፡ እንዲበዘብዟት ፡ ፈቀደላቸው ። ቫንዳሎችም ፡ ጨካኞች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ አጥፍተዋል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሮማ ፡ በተራዋ ፡ የተገዢነትን ፡ ቀንበር ፡ ተሸክማ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ኖረች ።

## የግሪኮችና ፡ የሮማውያን ፡ እምነት ።

ፉስቴል ፡ ደ ፡ ኩላንዥ ፡ የሚባለው ፡ ትልቁ ፡ የፈረንሣይ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ የግሪኮችንና ፡ የሮማውያንን ፡ እምነት ፡ ገልጦልናል ።

ባለፉት ፡ ክፍሎች ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ግሪኮችና ፡ ሮማውያን ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ታላቅ ፡ ሕዝቦች ፡ ሆነው ፡ ሳሉ ፡ በጣዖታት ፡ የሚያምኑና ፡ በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ የተሳሳቱ ፡ ሕዝቦች ፡ ነበሩ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከጥንት ፡ ጀምረው ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ሕይወት ፡ እንዳለው ፡ ያምኑ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሞት ፡ ለሰው ፡ ሕይወት ፡ መደምደሚያ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አያስቡም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ ከተለየች ፡ በኋላ ፡ ከመሬት ፡ ርቃ ፡ ሳትሄድ ፡ እዚሁ ፡ ትኖራለች ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ ከሥጋ ፡ ሳትለይ ፡ አብራ ፡ ተቀብራ ፡ የምትኖር ፡ ይመስላቸው ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በየጊዜው ፡ ለሞተ ፡ ሰው ምግብና ፡ መጠጥ ፡ እየወሰዱ ፡ ዘመዶቹ ፡ ከመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ያፈሱለታል ፡ ከሞተ ፡ በኋላም ፡ የሚበላና ፡ የሚጠጣ ፡ ይመስላቸው ፡ ነበርና ።

እንደዚሁም ፡ ልብሱን ፡ መሣሪያውንና ፡ የሚያስፈልገውንም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃ ፡ አብረው ፡ ይቀብሩ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ይጠቀሙት ፡ የነበሩ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ በመቃብር ፡ ውስጥ ፡ እንዲያገለግሉት ፡ በማለት ፡ እንስሳትንና ፡ ባሮችን ፡ ከመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ያርዷቸው ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የንጉሡ ፡ የፕሪያምን ፡ ልጅ ፡ ፖሊክሴን ፡ የምትባለውን ፡ የአሺል ፡ ምርኮኛ ፡ በመሆኗ ፡ በአሺል ፡ መቃብር ፡ ላይ ፡ አርደዋታል ።

ከሞተ ፡ በኋላ ፡ሬሳው ፡ ሳይቀበር ፡ የቀረ ፡ ሰው ፡ ነፍሱ ፡ ማረፊያ ፡ አጥታ ፡ ስትንከራተትና ፡ ስትቅበዘበዝ ፡ ትኖራለች ፡ ብለው ፡ ስለሚያምኑ ፡ ከሞት ፡ ይልቅ ፡ የሚፈሩት ፡ ሳይቀበሩ ፡ መቅረትን ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የሞተን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ በሚገባ ፡ አቀባበር ፡ መቅበር ፡ ትልቅ ፡ የሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ያገኛል ፡ ብለው ፡ አያምኑም ፡ ነበር ።



በኦዲሴ ፡ ውስጥ ፡ ዩሊስ ፡ በአስማት ፡ ከሞቱት ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ በተገናኘ ፡ ጊዜ ፡ ከአሺል ፡ ጋር ፡ ባደረገው ፡ ንግግር ።

«ቀድሞም ፡ በሕይወት ፡ ሳለህ ፡ እኛ ፡ አርጎሮኖች ፡ እንደ ፡ አማልክት ፡ እናከብርህ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ በሙታን ፡ ላይ ፡ ነግሠሃል ። አሺል ፡ ሆይ ፤ ስለዚህ ፡ በመሞትህ ፡ አትዘን ፡ » ሲል ፡ አጽናናው ።

አሺል ፡ ግን ፡ «ምንም ፡ በማይጠቅሙት ፡ በሙታን ፡ ላይ ፡ ከመንገሥ ፡ ቅርስ ፡ ለሌለው ፡ መናጢ ፡ ደሃ ፡ ገበር ፡ ሆኜ ፡ መሬት ፡ ማረስን ፡ ለጌታ ፡ መገዛትን ፤ እመርጣለሁ ። ስለዚህ ፡ በመሞቴ ፡ አታጥናናኝ ፡ »ሲል ፡ መልሶለታል ። ይህም ፤ ደግ ፡ ቢሠሩም ፡ ክፉ ፡ ቢሠሩም ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ምንም ፡ ተስፋ ፡ እንዳልነበራቸው ፡ ያስረዳናል ። በኋላ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ የሠሩና ፡ ደግ ፡ የሠሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ ዋጋቸውን ፡ ያገኛሉ ፤ አንዳንድ ፡ ባለ ፡ መልካም ፡ ምግባር ፡ የሆኑ ፡ ሰዎችም ፡ ፍጹም ፡ ደስታ ፡ ከሚገኝበት ፡ ያማልክት ፡ መኖሪያ ፡ ከሆነው ፡ ኤሊዜ ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ ይገባሉ ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበር ።

## የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ።

ባለፈው ፡ ታሪክ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ግሪኮች ፡ በጥበብ ፣ ሮማውያን ፡ ሕዝቦች ፡ በማስተዳደር ፡ ናላ ፡ ሆነው ፡ ዓለምን ፡ ሲመሩ ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱ ፡ ሲወድቁ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያልሠለጠኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ኃይላቸው ፡ ስለገነነ ፡ ዓለም ፡ ተመልሳ ፡ ወደ ፡ ድንቁርና ፡ ልትወድቅ ፡ የሚያሰጋት ፡ በሆነበት ፡ ሰዓት ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ብርሃን ፡ ይዛ ፡ ደረሰች ።

ይህም ፡ ሥልጣኔ ፡ እልም ፡ ድርግም ፡ ብላ ፡ ልትጠፋ ፡ ያስፈራችበት ፡ የሁከትና ፡ የጦርነት ፡ የድንቁርናና ፡ የጨለማ ፡ ጊዜ ፡ መካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ይባላል ።

የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ለኋለኛው ፡ ዓለም ፡ መሰናጃ ፡ ሆኖ ፡ የሰው ፡ ፍጻሜ ፡ ወይም ፡ የማያልቅ ፡ ደስታ ፡ ያለበት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፣ ወይም ፡ የማያልቅ ፡ ስቃይ ፡ ያለበት ፡ ገሃነም ፡ መሆኑን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ወንድማማቾች ፡ መሆናቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አለመበላለጣቸውን ፡ የዓለም ፡ ክብርና ፡ ሀብት ፡ ከንቱነቱን ፡ ውርደትና ፡ ድኅነት ፡ መልካም ፡ ምግባር ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጦ ፡ ባስተማረ ፡ ጊዜ ፡ የዓለምን ፡ ክብር ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ በሚቆጥሩበት ፡ ቄሣሮችም ፡ በየመቅደሱ ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ ይሰገድላቸው ፡ በነበረበት ፡ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ በሚታይበት ፡ መንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ እውነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያስተምረው ፡ ትምህርት ፡ ሲሰማ ፡ በዚያ ፡ ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ለመንፈስ ፡ ግራ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ ታያቸው ። እውነተኛውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ በመፈለግ ፡ ነፍሳቸው ፡ ተጠምታ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ሲሰሙ ፡ የአእምሮ ፡ ዓይናቸው ፡ ተከፈተ ።

ለምሳሌ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ በገባበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ መሥፍን ፡ ከኖርዘምቤርላንድ ፡ ንጉሥ ፡ ኤድዊ ፡ ከሚባለው ፡ ጋር ፡ ሲጫወት ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ይባላል ።



«ንጉሥ ፡ ሆይ ፣ በክረምት ፡ ወራት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚደርሰውን ፡ ነገር ፡ ሳታስታውሰው ፡ አትቀርም ። ከካፒቴኖችህና ፡ ከጦር ፡ ሰዎችህ ፡ ጋር ፡ ከገበታ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠህ ፡ ጥሩ ፡ እሳት ፡ ነዶ ፣ ቤቱ ፡ ሞቆ ፡ ከደጅ ፡ ግን ፡ ሲዘንብ ፣ በረዶ ፡ ሲጥልና ፡ ነፋስም ፡ ሲነፍስ ፡ አንዲት ፡ ትንሽ ፡ ወፍ ፡ እየበረረች ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ታልፋለች ፣ ባንዱም ፡ በር ፡ ገብታ ፡ ባንደኛው ፡ በር ፡ ትወጣለች ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የምታልፍበት ፡ ጊዜ ፡ ለሷ ፡ የደስታ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ዝናብና ፡ ነፋስ ፡ አያገኛትምና ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ አጭር ፡ ነው ፡ ወፍዋ ፡ በቅጽበት ፡ ዓይን ፡ ከክረምት ፡ ወጥታ ፡ ወደ ፡ ክረምት ፡ ተመልሳ ፡ ትገባለችና ፡ ሰዎችም ፡ በዚች ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የሚያሳልፍዋት ፡ ሕይወት ፡ እንደዚሁ ፡ መስሎ ፡ ይታየኛል ።

ከኋላና ፡ ከፊት ፡ ያለውንም ፡ የዘመን ፡ ረጅምነት ፡ ሲያስተያዩት ፡ የሕይወት ፡ ጊዜም ፡ የዚያኑ ፡ ያህል ፡ አጭር ፡ ነው ። ከሕይወት ፡ ኋላና ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ በጨለማና ፡ በሥጋት ፡ የተሸፈነ ፡ ነው ፡ መርምረን ፡ ልናውቀው ፡ ባለመቻላችን ፡ ሲያስጨንቀን ፡ ይኖራልና ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ አዲሱ ፡ ሃይማኖት ፡ ጥቂት ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሊያስተምረን ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፡ ልንከተለው ፡ ዘንድ ፡ የሚገባ ፡ ነው ። »

ለዓለም ፡ ክብርና ፡ ደስታ ፡ ይገዙ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያስተምረውን ፡ ትምህርት ፣ ሲሰሙ ፡ ቍጣቸው ፡ ነደደ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በኔሮንና ፡ በሌሎቹም ፡ ነገሥታት ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያኖች ፡ መሰደድና ፡ መገደል ፣ መወረስና ፡ መታሠር ፡ ደረሰባቸው ። ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ የመጣው ፡ የሮማ ፡ መንግሥት ፡ ሊወድቅ ፡ በተቃረበበት ፡ ጊዜ ፡ ስለነበረ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በመምጣቱ ፡ ምክንያት ፡ አማልክቶቻችን ፡ እንደተለመደው ፡ የሚያከብሩቸውና ፡ የሚሰግዱላቸው ፡ እየጠፉ ፡ ስለተረሱና ፡ ስለተናቁ ፡ ነው ፣ መንግሥታችን ፡ የደከመውና ፡ የፈረሰው ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ መእት ፡ አመጣብን ፡ እያሉ ፡ ዘለዓለም ፡ ያለም ፡ ገዢዎች ፡ ሆነው ፡ የሚኖሩ ፡ ይመስላቸው ፡ የነበሩ ፡ ሮማውያን ፡ ጥፋቱን ፡ በክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ ጣሉባቸው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሮማ ፡ መንግሥት ፡ የወደቀው ፡ ባለፉት ፡ ገጾች ፡ እንዳየነው ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ ያስተዳዳሪዎቹ ፡ ጠባይ ፡ በመበላሸቱ ፡ ነው ። ይልቅስ ፡ መንግሥቱ ፡ ባሸናፊዎቹ ፡ እጅ ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሸናፊዎች ፡ ሆነው ፡ የመጡትን ፡ አረመኔዎች ፡ በመገሠጽና ፡ በማስተማር ፡ እውቀትንና ፡ ጥበብን ፡ በየገዳሙና ፡ በያብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እየሰበሰበ ፡ በማኖር ፡ የትምህርትና ፡ የበጎ ፡ መንፈስ ፡ አድባር ፡ ሆና ፡ የሕዝቡን ፡ መንፈስ ፡ በመምራት ፡ ሥልጣኔ ፡ ጨርሳ ፡ ውድም ፡ ብላ ፡ እንዳትጠፋ ፡ አዳነቻት ።



## የመካከለኛው ፡ ዘመን ።

የመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ የሚባለው ፡ የሮማ ፡ መንግሥት ፡ ከሁለት ፡ ከተከፈለበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ፬፻፸፮ ፡ ዓ. ም. ቱርኮች ፡ የቍስጥንጥንያን ፡ ከተማ ፡ (ከያዙበት ፡ ፲፬፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ) ማለት ፡ የምሥራቁ ፡ የሮማ ፡ መንግሥት ፡ እፈረሰበት ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ነው ።

ባለፈው ፡ ታሪክ ፡ እንደተናገርነው ፡ የሮማን ፡ መንግሥት ፡ በጠፋት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕዝቦች ፡ ምክንያት ፡ አውሮፓ ፡ በጦርነት ፡ ስለተበጠበጠች ፡ ጥበብ ፡ እየጠፋች ፡ ሄደች ። ይልቁንም ፡ አቲላ ፡ የሚባለው ፡ ከእስያ ፡ የመጣ ፡ ጨካኝ ፡ ጦረኛ ፡ በረገጠው ፡ ቦታ ፡ ሁሉ እያቃጠለና ፡ እያዘረፈ ፡ ሕዝቡን ፡ በጭካኔ ፡ እየገደለ ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ አጠፋ ። ( ፈረሴ ፡ ባለፈበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ሣር ፡ አይበቅልበትም ፡) እያለ ፡ ይናገር ፡ ነበር ። በጭካኔው ፡ ምክንያት ፡ አውሮፓውያን ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅሠፍት ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።

ከጌታ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በ፭፻፸፩ ፡ ዓ. ም. ደግሞ ፡ መሐመድ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ በዓረብ ፡ አገር ፡ በመካ ፡ ከተማ ፡ ተወለደ ። እሱም ፡ የእስላምን ፡ ሃይማኖት ፡ መሥርቶ ፡ ዓለምን ፡ በሰይፍ ፡ ለማስለም ፡ ስላሰበ ፡ በዚህ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ዓለም ፡ በእስላሞች ፡ ጦር ፡ ተበጠበጠች ።

ከመሐመድ ፡ በኋላ ፡ የተነሡት ፡ ወራሾቹ ፡ የሆኑ ፡ ከሊፋዎች ፡ ሶርያን ፡ ግብፅን ፡ ፋርስን ፡ አሰለሙዋቸው ። ቀጥሎ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ እስከ ፡ ሕንድ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ የአፍሪካን ፡ የሰሜን ፡ ጠረፍ ፡ ይዘው ፡ እስከ ፡ እስፓኛ ፡ ዘለቁ ።

አውሮፓም ፡ በእስላሞች ፡ እጅ ፡ ልትወድቅ ፡ አስፈርቷት ፡ ነበር። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተወለደበትንና ፡ ወንጌል ፡ ያስተማረበትን ፡ የሞተበትንና ፡ የተቀበረበትንም ፡ ቅድስት ፡ አገር ፡ ሊሳለሙ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የሚሄዱትን ፡ ክርስቲያኖች ፡ እስላሞች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ ስላንገላቱዋቸውና ፡ ግፍ ፡ ስለሠሩባቸው

በዚህ ፡ የተነሣ ፡ የአውሮፓ ፡ ክርስቲያን ፡ መንግሥታትና ፡ እስላሞች ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ተዋጉ ። ይኸውም ፡ የመስቀል ፡ ጦርነት ፡ ይባላል ።

በኋላ ፡ ግን ፡ እስላሞች ፡ የጌጥ ፡ የደስታና ፡ የምቾት ፡ አኗኗር ፡ የስንፍናም ፡ ፍቅር ፡ ስላደረባቸው ፡ እየደከሙ ፡ ሄዱ ።

የእስላሞች ፡ ኃይል ፡ እየደከመ ፡ መሄድ ፡ በጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ ለምሳሌ ፡ በደማስቆስ ፡ ከሊፋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ምቾትና ፡ ጌጥ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። እዚያ ፡ ሄዶ ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ የግሪክ ፡ አምባሳደር ፡ ያየውን ፡ ሲናገር ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ዝርዝር ፡ ሰጠ ። በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ሠላሳ ፡ ስምንት ፡ ሺህ ፡ ስጋጃዎች ፡ ይነጠፉሉ ። ከእነዚሁም ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ በሐር ፡ የተሠሩና ፡ በወርቅ ፡ የተጠለፉ ፡ ናቸው ። ሃያ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ለእግር ፡ መርገጫ ፡ የሚሆኑ ፡ ናቸው ። ከሊፋው ፡ መቶ ፡ አንበሶች ፡ አሉት ። ለያንዳንዶቹም ፡ አንዳንድ ፡ ጠባቂ ፡ ሰው ፡ ተደርጎላቸዋል ። ከሚታዩትም ፡ የጌጥ ፡ ዕቃዎች ፡ መካከል ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ዛፍ ፡ ከዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ ዛፍ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ትልልቅ ፡ ቅርንጫፎች ፡ አሉት ። በእነዚህም ፡ ቅርንጫፎችና ፡ በታናናሾቹም ፡ ቅርንጫፎች ፡ ላይ ፡ በያይነቱ ፡ ወፎች ፡ ይታያሉ ። የዛፉ ፡ ቅርንጫፎችና ፡ ቅጠሎች ፤ ወፎቹም ፡ የተሠሩት ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ ነው ።

ዛፉ ፡ ነፋስ ፡ እንደሚያወዛውዛቸው ፡ እንደ ፡ ጫካ ፡ ዛፎች ፡ እየተወዛወዘ ፡ በላዩ ፡ የሠፈሩት ፡ ወፎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ድምፅ ፡ ሲጮሁ ፡ (ሲዘፍኑ) ይሰማሉ ። በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጌጥ ፡ መካከል ፡ አምባሳደሩ ፡ በቪዚሩ ፡ መሪነት ፡ ወደ ፡ ከሊፋው ፡ ዙፋን ፡ ቀርቦ ፡ ተገናኘ ።

በእስፓኝ ፡ አገር ፡ የነበሩት ፡ እስላሞች ፡ ደግሞ ፡ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ የባሱ ፡ እንጂ ፡ የተሻሉ ፡ አልነበሩም ።

ትልቁና ፡ ሦስተኛው ፡ አብዱልራህማን ፡ የሚባለው ፡ ሡልጣን ፡ ከኮርዶ ፡ ከተማ ፡ አጠገብ ፡ ለሚወዳት ፡ ሚስቱ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የአትክልት ፡ ቦታ ፡ የሚገኝባትን ፡ ዘኅራ ፡ የምትባለውን ፡ ከተማ ፡ ሠራላት ። ለዚህም ፡ ሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ሚሊዮን ፡ ስተርሊንግ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ አወጣ ። ሥራውም ፡ ያለቀው ፡ በሃያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ነው ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ የታወቁትን ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ሐውልት ፡ የሚቀርፁ ፡ ሰዎችና ፡ (የአርሺቴክቱር) መሐንዲሶች ፡ አስፈልጎ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ከቍስጥንጥንያ ፡ አስወሰዳቸው ።



ለቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ምሰሶና ፡ ጌጥ ፡ የሚሆኑ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ የእብነ ፡ በረድ ፡ ዓምዶች ፡ ከእስፓኝ ፤ ከአፍሪካ ፤ ከግሪክ ፤ ከኢጣሊያ ፡ አገሮች ፡ አስወሰደ ። የእንግዳ ፡ መቀበያው ፡ አዳራሽ ፡ በወርቅና ፡ በፊርጥ ፡ ጌጥ ፡ የተሸለመ ፡ ነበር ። ሚስቶቹ ፤ ቁባቶቹ ፡ ሸንቅሎች ፡ ስልቦች ፡ ቁጥራቸው ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ይሆን ፡ ነበር ።

አብዱልራህማን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በእጁ ፡ የጻፈው ፡ አንድ ፡ ማስታወሻ ፡ ተገኘ ። በዚሁም ፡ ማስታወሻ ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ይነበብበት ፡ ነበር ።

«አሁን ፡ እነሆ ፡ ከአምሳ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ሁልጊዜ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ሆኜ ፡ ወይም ፡ በሰላም ፡ አርፌ ፡ በንጉሥነት ፡ ኖርኩ ። ዜጎቼ ፡ ይወዱኛል ። የምመኘውን ፡ ያህል ፡ ሀብትና ፡ ክብር ፤ ኃይልና ፡ ደስታ ፡ አገኘሁ ። ለደስታዬ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ የጐደለ ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ድርሻ ፡ ሆነው ፡ የተሰጡኝን ፡ የደስታዬን ፡ ቀኖች ፡ በጥንቃቄ ፡ ቆጠርኋቸው ። እነዚሁም ፡ የደስታዬ ፡ ቀኖች ፡ ከአሥራ ፡ አራት ፡ ይደርሳሉ ። . . . . . . ሰው ፡ ሆይ ፤ ተስፋህን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ አታድርግ ። »

ይህን ፡ ለመሰለ ፡ ትርፍ ፡ ለሌለው ፡ ደስታ ፡ ሀብታቸውንና ፡ ጊዜያቸውን ፡ በከንቱ ፡ እያባከኑ ፡ እስላሞች ፡ ኃይላቸውና ፡ ሥልጣኔያቸው ፡ እያደገ ፡ በመሄድ ፡ ፈንታ ፡ ባጭር ፡ ተቋረጠ ።

እስፓኛን ፡ ይገዙ ፡ የነበሩ ፡ እስላሞች ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ውብ ፡ የሆነችውን ፡ ግረናድ ፡ የምትባለውን ፡ ከተማ ፡ ለቀው ፡ ሲወጡ ፡ ንጉሡ ፡ ቦአብዲል ፤ ወይም ፡ አቡ ፡ አብዱላህ ፡ የሚባለው ፡ ከተማዋን ፡ እያየ ፡ አለቀሰ ። እናቱም ፡ ይህን ፡ ተመልክታ ፡ «በወንድነት ፡ ተከላክለህ ፡ ለማዳን ፡ ያልቻልከውን ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ አልቅስለት ፡ » አለችው ፡ ይባላል ።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ በፍልስፍና ፡ በሕክምና ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ጥበብ ፡ በሒሣብ ፡ ትምህርት ፡ ይልቁንም ፡ በአልጀብር ፡ የሠለጠኑ ፡ ነበሩ ።

እንደዚሁም ፡ በኢንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ የሱፍና ፡ የሀር ፡ በያይነቱ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ጨርቅ ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ አውሮፓውያን ፡ የሚሠሩበትን ፡ የቍጥር ፡ አኃዞች ፡ የወሰዱት ፡ ከአረቦች ፡ ነው ።

ታሜርላን ፡ (ቲሙርሌንግ ፡ )የሚባል ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ትልቅ ፡ ጦረኛ ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፡ በሞንጎል ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ከመሠረተ ፡ በኋላ ፡ እስላሞች ፡ ኃይል ፡ አግኝተው ፡ ዓለምን ፡ በስጨነቁበት ፡ ዘመን ፡ ባያዜት ፡ ከሚባለው ፡ ከኦቶማን ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ተጋጭተው ፡ የኦቶማኑ ፡ ንጉሥ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ወታደሮች ፡ የሞንጎሉ ፡ ንጉሥ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ወታደሮች ፡ ይዘው ፡ ባደረጉት ፡ የሚያስፈራ ፡ ውጊያ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ከተራረዱ ፡ በኋላ ፡ የኦቶማኑ ፡ ንጉሥ ፡ ባያዜት ፡ ተማረከ ። እሱም ፡ በክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ቀጣው ፡ ብለው ፡ ክርስቲያኖች ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ታሜርላን ፡ (ቲሙርሌንግ ፡ )ጨካኝ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ በእስላሞች ፡ ከተማ ፡ በባግዳድ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ሲገባ ፡ ሰማኒያ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ አረደ ። ጭንቅላታቸውንም ፡ ሰብስቦ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ እየቆለለ ፡ ፒራሚድ ፡ የሚመስሉ ፡ መቶ ፡ ሐያ ፡ ሐውልቶች ፡ ሠራበት ። ቱርኬስታን ፡ ፋርስ ፡ ሜዞጶታሚያ ፡ አርሜንያ ፡ መስኮብ ፡ ፖሎኝ ፡ እነዚህ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ጨካኝ ፡ ጦረኛ ፡ እጅ ፡ ወድቀው ፡ ብርቱ ፡ ጥፋት ፡ አግኝቷቸዋል ።



## ባርነት ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ።

ሮማ ፡ ግዛቷን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለማስፋፋት ፡ ጦርነት ፡ ታደርግ ፡ በነበረችበት ፡ ዘመን ፡ ባለፈው ፡ ታሪክ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ድል ፡ የሆኑትን ፡ ሕዝቦች ፡ ባሮች ፡ ታደርጋቸው ፡ ስለነበር ፡ ባርያ ፡ መግዛትና ፡ መሸጥ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ምዕራባዊው ፡ የቄሣር ፡ መንግሥት ፡ ከመውደቁ ፡ በፊት ፡ በነበሩት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ባርነት ፡ እየቀረ ፡ ሄደ ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ የሰዎች ፡ አእምሮ ፡ እየታደሰ ፡ በባርነት ፡ የሚኖሩትም ፡ ሰዎች ፡ እንደሌላው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ ከሆነው ፡ ከዳም ፡ የተፈጠሩ ፡ በመሆናቸው ፡ ወንድሞችነታቸውን ፡ እያሳሰባቸው ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ መቆጠራቸው ፡ ቀርቶ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚገባው ፡ የነፃነት ፡ መብት ፡ ሊሰጣቸው ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ዓለም ፡ ስለተገነዘበው ፡ ነው ። ባንድ ፡ በኩልም ፡ ደግሞ ፡ ሮማ ፡ ድል ፡ እያደረገች ፡ አገር ፡ የመያዙ ፡ ሥራ ፡ ስለቀረ ፡ ነው ። በጥንት ፡ ዘመን ፡ ባርነት ፡ እንዲቀር ፡ የተከራከሩ ፡ ሴኔክን ፡ የመሰሉ ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተዋል ።

የሞንጎል ፡ ጦር ፡ ተነሥቶ ፡ አውሮፓ ፡ ዳር ፡ ባለው ፡ በምሥራቅ ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ የሚገኙትን ፡ አገሮች ፡ እየተመላለሰ ፡ ከግብፅ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መስኮብ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ በወጋበትና ፡ በወረረበት ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ምርኮኞችና ፡ ስደተኞች ፡ ሰዎች ፡ በቱርኮች ፡ እጅ ፡ ወድቀዋል ። እነሱም ፡ ከጥቁር ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ከሚገኙት ፡ ገበያዎች ፡ እየወሰዱ ፡ ሸጠዋቸዋል ። ከዚያም ፡ ያውሮፓ ፡ ሰዎች ፡ ከሜዲቴራኔ ፡ ወደቦች ፡ ላይ ፡ እየወሰዱ ፡ በውድ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጧቸው ፡ ነበር ።

እየገዙ ፡ ይነግዱባቸው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ የቬኒሲያና ፡ የጄኖቫ ፡ ሰዎች ነበሩ ። እነዚህም ፡ ባሮች ፡ የአርመን ፡ የሰርያ ፡ የቡልጋሪያ ፡ የሴርቢያ ፡ ሰዎች ፡ መስኮቦችና ፡ ታርታሮችም ፡ ነበሩ ። በዚሁ ፡ ዘመን ፡ አቅራቢያ ፡ የዓረብ ፡ ነጋዴዎች ፡ የሱዳንን ፡ ጥቁሮች ፡ በሰሃራ ፡ በረሃ ፡ በኩል ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ማሮክና ፡ ወደ ፡

እስፓኛ ፡ እያስተላለፉ ፡ ሸጠዋቸዋል ። በክርስቲያኖችና ፡ በእስላሞች ፡ መካከል ፡ ስለኢየሩሳሌም ፡ ጉዳይ ፡ በረጅም ፡ ዘመናት ፡ ውስጥ ፡ በተደረጉት ፡ የመስቀል ፡ ጦርነቶች ፡ ምክንያት ፡ ቱርኮች ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ የማረኳቸውን ፡ ሮፓውያን ፡ ባሮች ፡ አድርገው ፡ ያኖርዋቸው ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በእስላሞች ፡ ዘንድ ፡ ነጭ ፡ ባርያ ፡ መግዛት ፡ ተለመደ ። ኋላም ፡ ለሞሪታኒያ ፡ አገር ፡ እስላሞች ፡ የቬኒሲያ ፡ ሰዎች ከአድሪያቲክ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ከሚዋሰኑት ፡ አገሮች ፡ የሚገኙትን ፡ የእስላቭ ፡ ዘር ፡ የሆኑትን ፡ ነጮች ፡ እያፈኑ ፡ ይሸጡዋቸው ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ራሳቸው ፡ እስላሞቹ ፡ በሜዲቴራኔ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ ሕዝቦች ፡ በየጊዜው ፡ አፍነው ፡ እየወሰዱ ፡ ሲገዟቸው ፡ ኖረዋል ። ይህንንም ፡ የባርያ ፡ ፈንጋይነት ፡ ሥራ ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ይሠሩት ፡ ነበር ።

ወደፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ የአሜሪካ ፡ አገር ፡ ተገኝቶ ፡ ሮፓውያን ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ መያዝ ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ፡ ስለባርያ ፡ ጉዳይ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ ተፈጠረ ። ዓለም ፡ በሥልጣኔ ፡ መንፈስ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ የማሻሻሉን ፡ ሥራ ፡ ትቶ ፡ ብዙ ፡ መንግሥታት ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ፡ በተገኙት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ያላቸውን ፡ ጥቅም ፡ ለማስፋፋት ፡ ሲሉ ፡ እንደገና ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሰው ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ጀመር ። በአሜሪካ ፡ አገር ፡ የነበሩት ፡ ዘራቸው ፡ ሕንድ ፡ የሆነ ፡ ያገሩ ፡ ተወላጆች ፡ ሮፓውያን ፡ አገራቸውን ፡ በያዙባቸው ፡ ጊዜ ፡ የእርሻና ፡ የቁፋሮ ፡ ሥራ ሊያሠሩዋቸው ፡ ጀምረው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በመለገም ፡ ወይም ፡ ጉልበታቸው ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ያልተሰጠ ፡ በመሆኑ ፡ ይህን ፡ በመሰለው ፡ ድካም ፡ ደስ ፡ በማያሰኝ ፡ አኳኋን ፡ ሊሠሩላቸው ፡ ሳይችሉ ፡ ቀሩ ።

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ካውሮፓ ፡ እየተሰደዱ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ ይሄዱ ፡ የነበሩት ፡ ደሆች ፡ ሠራተኞች ፡ ለመንገዳቸው ፡ ከሚሩ ፡ የሚከፍሉት ፡ ገንዘብ ፡ ስላልነበራቸው ፡ እየሠሩ ፡ እንዲከፍሉ ፡ በሚዋዋሉት ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ይህንኑ ፡ የአታክልት ፡ ሥራ ፡ ያሠሩዋቸው ፡ ነበር ። ይህም ፡ የተባለው ፡ የአታክልት ፡ ሥራ ፡ ያገሩ ዋና ፡ ሀብት ፡ የሆኑትን ፡ የሸንኮር ፡ አገዳና ፡ ጥጥ ፡ መትከል ፡



ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ የተገኙት ፡ ሠራተኞች ፡ ቁጥራቸው ፡ ያነሰና ፡ ሥራቸውም ፡ የማያጠግብ ፡ ሆኖ ፡ ባለቤቶቹ ፡ በሚፈልጉት ፡ መጠን ፡ የበቃ ፡ ጥቅም ፡ ስላላገኙበት ፡ የጥቁር ፡ ባርያ ፡ ጉዳይ ፡ ባዲስ ፡ ሁኔታ ፡ ተወለደ ።

ባርነት ፡ የነበረው ፡ በሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ስለሆነ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ ክብር ፡ የሚደረገው ፡ ይህ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የአእምሮ ፡ አስተያየት ፡ በሰዎች ፡ መንፈስ ፡ ተቀርጾ ፡ ፍሬ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ አስፈልጎታል ። ለምሳሌ ፡ በመስኮብ ፡ አገር ፡ ባሮች ፡ ነፃነት ፡ ያገኙት ፡ በቀዳማዊ ፡ ኒኮላ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። ፲፰፻፴፫—፲፰፻፷፫ ዓ. ም. ።

ያውም ፡ ቢሆን ፡ በባርነት ፡ ስም ፡ የሚቀበሉት ፡ ከባድ ፡ የሆነው ፡ የጭከኔ ፡ ቀንበር ፡ ቀርቶላቸው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ተሻሻለላቸው ፡ እንጂ ፡ ባገልጋይነት ፡ ለጌቶቻቸው ፡ እየሠሩ ፡ መኖራቸው ፡ አልቀረም ፡ ነበር ። ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ የተሰጣቸው ፡ ግን ፡ በ፲፰፻፷፩ ፡ ዓ. ም. በዳግማዊ ፡ አሌክሳንድር ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ።

## ዳግም ፡ ልደት ።

የሥልጣኔ ፡ ምንጩ ፡ ግሪክ ፡ ነች ፡ ብለናልና ፡ እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ እንዴት ፡ እንደተሸጋገረች ፡ እናስተውል ። ግሪክና ፡ ሮማ ፡ ሲወድቁ ፡ ዓለም ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ዓመታት ፡ የሚሆን ፡ በድንቁርና ፡ ካንቀላፋች ፡ በኋላ ፡ የሥልጣኔ ፡ መንፈስ ፡ እንደገና ፡ ለምልሞ ፡ አበበ ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ጊዜ ፡ «ዳግም ፡ ልደት ፡ » ተባለ ። (ትርጉሙም ፡ ሁለተኛ ፡ መወለድ ፣ ተመልሶ ፡ መፈጠር ፣ እንደገና ፡ መታደስ ፡ እንደማለት ፡ ያህል ፡ ነው ። ) ይህ ፡ የሆነውም ፡ ባሥራ ፡ አምስተኛው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ምክንያቶቹም ፡ ቱርኮች ፡ ቁስጥንጥንያን ፡ ሲይዙ ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ የነበሩ ፡ የግሪክ ፡ ሊቃውንት ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ተሰደው ፡ ገብተው ፡ ለአውሮፓውያን ፡ ጥበብን ፡ በማስተማራቸው ፣ የመርከብ ፡ አሠራር ፡ ጥበብም ፡ በጣም ፡ ተሻሽሎ ፡ በመስፋፋቱ ፣ የማተሚያ ፡ ጥበብም ፡ ተገኝቶ ፡ መጻሕፍት ፡ በብዙ ፡ እየታተሙ ፡ ለሕዝብ ፡ በመዳረሳቸውና ፡ ዕውቀት ፡ ለሰዎች ፡ በመገለጡ ፡ ከላበት ፡ ኃይል ፡ የሚገኘውም ፡ አገልግሎት ፡ በመታወቁ ፡ ነው ።

ቀድሞ ፡ መጽሐፍ ፡ ብርቅ ፡ ነበር ። የሚጻፈውም ፡ በእጅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ለመግዛት ፡ የሚችሉ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። የማተሚያ ፡ ቤት ፡ ጥበብ ፡ ሲገኝ ፡ ግን ፡ መጻሕፍት ፡ በብዙ ፡ እየታተሙ ፡ ሰዎች ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ ገዝተው ፡ ትምህርት ፡ ለማግኘትና ፡ ጥበብ ፡ ለመመርመር ፡ ቻሉ ።

ለመርከበኞች ፡ መሪ ፡ የሚሆን ፡ የቡሶል ፡ ዘዴ ፡ በመገኘቱ ፡ መርከቦቹ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሊመላለሱ ፡ ቻሉ ።

ባሩድም ፡ ስለተገኘ ፡ የመድፍና ፡ የጠመንጃ ፡ መሣሪያ ፡ ተሠራ ፣ በሚከተለው ፡ አርዕስት ፡ እንደምናገኘው ፡ ሳይታወቅ ፡ ይኖር ፡ የነበር ፡ የአሜሪካ ፡ አገር ፡ ተገኘ ። በመስቀል ፡ ጦርነቶች ፡ ምክንያት ፡ አውሮፓውያን ፡ ሀብትን ፡ ከውሮፓ ፡ ውጭ ፡ ሄደው ፡ ለመፈለግ ፡ አሳባቸው ፡ ተነሣሣ ። ፈረንሳይና ፡ እንግሊዝም ፡ ከሮማ ፡ ቀንበር ፡



ወጥተው ፡ ነፃነታቸውን ፡ ካገኙ ፡ በኋላ ፡ እንግሊዞች ፡ ከፈረንሣይ ፡ አገር ፡ ገብተው ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ጦርነት ፡ የሚባለውን ፡ ተዋጉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ ተዳክመው ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያሉ ፡ በኃይል ፡ በሥልጣኔ ፣ በሀብት ፡ ደረጁ ። ሊቃውንቶቻቸውም ፡ ከቍስጥንጥንያ ፡ ከመጡት ፡ ከግሪክ ፡ መምህራን ፡ ዘንድ ፡ እየተጠጉ ፡ የግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ተምረው ፡ የጥንቱን ፡ ዕውቀት ፡ ይመረምሩ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ዕውቀት ፡ ለሰዎች ፡ ተገለጠላቸው ።

ሮጀር ፡ ቤከን ፡ በፍልስፍና ፣ ሌዎናርዶ ፡ ዳ ፡ ቪንቺ ፡ ሰፌ ፡ በሆነ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበብ ፣ ኮፔርኒክና ፡ ጋሊሌዎ ፡ በከዋክብት ፡ ጥበብ ፣ (አስትሮኖሚ ) ጂልበርት ፡ በማኘቲስምና ፡ በኤሌስትሪሲቴ ፡ አንድሬ ፡ ቬዛል ፡ በአናቶሚ ፣ ሃርቬ ፡ በደም ፡ መዘዋወር ፡ ምርመራ ፣ ጥበብን ፡ እየመረመሩና ፡ እየገለጡ ፡ ሄዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊቃውንት ፡ ጥበብን ፡ መጻሕፍትን ፡ በመመልከትና ፡ በፍልስፍና ፡ በመመራመር ፡ በመከራከርም ፡ ጊዜን ፡ ማሳለፍ ፡ የማይጠቅም ፡ ሆኖ ፡ ስላገኙት ፡ የሰው ፡ ድካምና ፡ ችግር ፡ በጥበብ ፡ እየተሻሻለና ፡ እየቀለለ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉበትን ፡ መንገድ ፡ ይፈልጉ ፡ ጀመር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የመኪና ፡ ጥበብ ፡ ተገኘ ።

ሮጀር ፡ ቤከን ፡ ይህንኑ ፡ ስለተገነዘበው ፡ «የጥበብና ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት (ናቱር ) የተሠወሩ ፡ የምሥጢር ፡ ሥራዎች » ብሎ ፡ በሰየመው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አስቀድሞ ፡ ተናግሮዋል ። ያለ ፡ ሰው ፡ በራሳቸው ፡ ብቻ ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ እየመራቸው ፡ ብዙ ፡ ቀዛፊዎች ፡ ከሞሉባቸው ፡ መርከቦች ፡ ይበልጥ ፡ ፍጥነት ፡ ያላቸው ፡ መርከቦች ፡ መሥራት ፡ ይቻላል ። በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ደግሞ ፡ ሠረገላዎች ፡ በከብቶች ፡ መጐተታቸው ፡ ቀርቶ ፡ መጠን ፡ በሌለው ፡ ፍጥነት ፡ እንዲሮጡ ፡ ተደርጎ ፡ መሥራት ፡ ይቻላል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በመኪናው ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጦ ፡ እየዘወረና ፡ እየመራው ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ አየሩን ፡ ሰንጥቆ ፡ የሚበር ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ የሚያንዣብብ ፡ መኪና ፡ መሥራትም ፡ ይቻላል ፡ » እነሆ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ንግግር ፡ ቤከን ፡ የሰው ፡ መንፈስ ፡ በመመራመር ፡ ብዛት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጡ ፡ መኪናዎች ፡ ለመሥራት ፡ የሚ

ችል ፡ መሆኑን ፡ ገለጠ ። ነገር ፡ ግን ፡ በሱ ፡ ዘመን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ምኞት ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ደፍሮ ፡ ይህን ፡ በመናገሩ ፡ እንደ ፡ ጠንቋይ ፡ ቆጠሩት ። በኋላ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ቆይቶ ፡ ስቴፈንስን ፡ ተወልዶ ፡ ባቡር ፡ በመሥራቱ ፡ ቤከን ፡ የተናገረውን ፡ ትንቢት ፡ በሥራ ፡ ፈጸመው ።

ሰዎች ፡ ጥበብን ፡ በመመርመር ፡ የሰውን ፡ ችግርና ፡ ድካም ፡ ለማቃለል ፡ የሚቻልበትን ፡ ጥቅም ፡ ያለውን ፡ አገልግሎት ፡ ለማግኘት ፡ እንዴት ፡ እንደተጣጣሩ ፡ ባጭሩ ፡ እንመልከተው ።

አርኪታስ ፡ የሚባል ፡ የፒታጐር ፡ ተማሪ ፡ የፕላቶን ፡ ወዳጅ ፡ የነበረ ፡ ፈላስፋ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በርሮ ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ ስታንዣብብ ፡ የምትቆይ ፡ አንዲት ፡ ርግብ ፡ ሠርቶ ፡ ነበር ።

ትልቁ ፡ አልቤር ፡ የሚባል ፡ በ፲፩፻፺፫ ፡ ዓ. ም. ተወልዶ ፡ በ፲፪፻፹ ፡ ዓ. ም. የሞተ ፡ አልሺሚ ፡ የሚመረምር ፡ መነኩሴ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውንም ፡ ሥራ ፡ እየሠራና ፡ ሲያናግሩትም ፡ መልሶ ፡ እየተናገረ ፡ እንግዳ ፡ ከውጭ ፡ መጥቶ ፡ በር ፡ ሲመታ ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ እንግዳውን ፡ ተቀብሎ ፡ ከማረፊያ ፡ ቤት ፡ የሚያስቀምጥ ፡ በመኪና ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ አሽከር ፡ ሠርቶ ፡ ነበር ።

ሬጂዎሞንታኒስ ፡ የሚባል ፡ ሊቅ ፡ እየበረረች ፡ ተነሥታ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ከዞረች ፡ በኋላ ፡ ተመልሳ ፡ መጥታ ፡ እጁ ፡ ላይ ፡ የምትቀመጥ ፡ ዝንብ ፡ ሠርቶ ፡ ነበር ። ባሮን ፡ ኬምፕለን ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ሠንጠረዥ ፡ የሚጫወት ፡ የመኪና ፡ ሰው ፡ ሠርቶ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ የመኪና ፡ ሰው ፡ በ፲፯፻፷፱ ዓ. ም. ሸንብሩን ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ ከና ፖሊዎን ፡ ጋር ፡ ሠንጠረዥ ፡ ተጫውቷል ።

ቦካንሶን ፡ የሚባል ፡ የፈረንሳዊ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ሚካኒሲያን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘፈን ፡ በዋሽንት ፡ የሚጫወት ፡ ሰው ፡ በመኪና ፡ ሠርቷል ። እንደዚሁም ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ የምትዋኝ ፤ የምትበላ ፤ የበላችውም ፡ ምግብ ፡ በአንጀቷ ፡ ውስጥ ፡ ተዋህዶ ፡ ገላ ፡ የሚሆናት ፡ አንዲት ፡ የመኪና ፡ ዳክዬ ፡ ሠርቶ ፡ ነበር ።

ይህችን ፡ ዳክየ ፡ በዓይናቸው ፡ ካዩዋት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ተመልካች ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጽፏል ። «ዳክዬይቱ ፡ በእግሮቿ ፡ ቆማ ፡ መንቀሳቀስ ፡ ትጀምራለች ፡ ጥቂት ፡ ከሄደች ፡ በኋላ ፡



ቆማ ፡ እግሮቿንና ፡ ክንፎቿን ፡ ራሷንም ፡ ታንቀሳቅሳለች ፤ ከዚያም ፡ እንደገና ፡ መሄድ ፡ ትጀምርና ፡ የምትበላው ፡ ጥራጥሬ ፡ ትፈልጋለች ። አንገቷንም ፡ ወደላይ ፡ መዛ ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ በርራ ፡ ትገባለች ፡ ከዚያም ፡ እየዋኘች ፡ ወደ ፡ ውስጥም ፡ እየጠለቀች ፡ ውሃ ፡ እየጠጣች ፤ ዓሣ ፡ እየያዘች ፤ በውሃው ፡ ውስጥ ፡ ትንደፋደፋለች ። በኩሬው ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ እያደረገች ፡ በሁሉም ፡ በኩል ፡ ተመላልሳ ፡ ከዳረሰችውና ፡ ነፍስ ፡ ያላት ፡ እውነተኛ ፡ ዳክዬ ፡ የምታደርገውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ካደረገች ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኩሬው ፡ ዳር ፡ ተጠግታ ፡ ከውሃው ፡ ውስጥ ፡ ትወጣለች ። ክንፎቿንም ፡ አራግፋ ፡ ጥቂት ፡ ትሄድና ፡ ትቆማለች ። ባንድ ፡ እግርዋ ፡ ብቻ ፡ ቆማ ፡ ሁለተኛው ፡ እግርዋን ፡ ወደላይ ፡ ታነሣና ፡ ክንፎቿን ፡ ታክለች ። ከላባዋም ፡ አንዳንዱ ፡ ሲወድቅ ፡ ይታያል ። ከዚያም ፡ እየሄደች ፡ የሚበላ ፡ ነገር ፡ ትፈልጋለች ። የፈሰሰላት ፡ ጥራጥሬ ፡ ካለበት ፡ ቦታ ፡ ስትደርስ ፡ እየለቀመች ፡ ከዋጠችው ፡ በኋላ ፡ ግማሹ ፡ እየተዋሃዳት ፡ ከሆዷ ፡ ውስጥ ፡ ሲቀር ፡ የቀረው ፡ ኩስ ፡ ሆኖ ፡ ይወጣል ።»

እነዚህ ፡ አቶማቶች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ እንደመጫዎቻ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ነገሮች ፡ ቢሆኑ ፡ የሰው ፡ አሳብ ፡ በጥበብ ፡ ሊመራ ፡ የጀመረበትን ፡ አዲስ ፡ መንገድ ፡ የሚያመለክቱ ፡ በመሆናቸው ፡ ዋጋ ፡ አላቸው ።

እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ስንመለከት ፡ ባገራችን ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የፈረንጅ ፡ ቋንቋ ፡ መናገር ፡ ብቻ ፡ ምን ፡ ይጥቅማል ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ክብሪትና ፡ መርፌ ፡ እንኳ ፡ ሠርታችሁ ፡ አላሳያችሁንም ፡ እያሉ ፡ የተማሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሲወቅሱ ፡ የምንሰማቸው ፡ የተገባ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ኑሮውን ፡ የሚያሻሽልበት ፡ የመኪና ፡ ዘዴ ፡ ለመሥራት ፡ ሲያስብ ፡ ታይቶ ፡ አልታወቀም ። አሁን ፡ ግን ፡ የእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ «ተግባረ ፡ እድ ፡» ያለ ፡ እየተጨመረ ፡ ሄዶ ፡ ባገራችን ፡ የመኪና ፡ ጥበብ ፡ እንዲለመድና ፡ እንዲስፋፋ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

ይህም ፡ ስለተባለ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ፋብሪካ ፡ ማቋቋም ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ይመስላቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ማወቅ ፡ ይገባል ።

ለምሳሌ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ቤንዚን ፡ የሚያነጥር ፡ አንድ ፡ ፋብሪካ ፡ ለማቆም ፡ ግማሽ ፡ ሚሊያርድ ፡ ማለት ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ፍራንክ ፡ ፈጅቷል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ማንኛውም ፡ አገር ፡ እንዳቅሙ ፡ መጠን ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሊኖረው ፡ ስለሚችል ፡ ሕዝባችን ፡ መንፈሱ ፡ ወደ ፡ መኪና ፡ ጥበብ ፡ እንዲሳብ ፡ ማድረግ ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።

የመኪና ፡ ጥበብ ፡ እየተስፋፋ ፡ ሲሄድ ፡ ፋብሪካ ፡ ተወለደ ። በእንዴት ፡ ያለ ፡ እርምጃ ፡ ተከናውኖ ፡ ፋብሪካ ፡ አሁን ፡ ካለንበት ፡ ዘመን ፡ እንደደረሰ ፡ ወደፊት ፡ በሚገኘው ፡ አርእስቱ ፡ እናስተውለዋለን።



## ባሮች ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ።

ክሪስቶፍ ፡ ኮሎምብ ፡ ያሜሪካን ፡ አገር ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ ይህንኑ ፡ አገር ፡ መጀመሪያ ፡ እስፓኞ ፡ ስትገዛው ፡ ቆየች ። በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ ግማሹን ፡ አገር ፡ እንግሊዞች ፡ ያዙት ። እንግሊዞች ፡ ከሰሜን ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ሲይዙ ፡ እስፓኞ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ከሚገኙት ፡ አውራጃዎች ፡ ይዛ ፡ ነበር ።

ክሪስቶፍ ፡ ኮሎምብ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ዓለምን ፡ በመርከብ ፡ ለመዞር ፡ አስቦ ፡ ከፖርቱጋልና ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ እርዳታ ፡ ቢጠይቅ ፡ የሚሰማው ፡ አጣ ። እስላሞች ፡ ተሸንፈው ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ የነበረችው ፡ የእስፓኞ ፡ ንግሥት ፡ ኢዛቤል ፡ የምትባለው ፡ ደግና ፡ ብልህ ፡ ሴት ፡ ስለነበረች ፡ መርከብና ፡ ጭፍሮች ፡ ስንቅም ፡ ሰጥታ ፡ ረዳችውና ፡ ወደ ፡ አሰበው ፡ መንገድ ፡ እንዲሄድ ፡ ፈቀደችለት ።

ክሪስቶፍ ፡ ኮሎምብ ፡ ብዙ ፡ አስቦ ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ዓለም ፡ ክብ ፡ መሆኗን ፡ በማስተዋል ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ዞሮ ፡ ከሕንድ ፡ አገር ፡ ለመድረስ ፡ እንደሚቻል ፡ ተረዳ ። አንድ ፡ ወር ፡ ከአሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ከተጓዘ ፡ በኋላ ፡ ካሰበው ፡ አገር ፡ ደረሰ ። ይህም ፡ አዲስ ፡ ዓለም ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ። ክሪስቶፍ ፡ ኮሎምብ ፡ ግን ፡ የደረሰው ፡ ከሕንድ ፡ አገር ፡ መስሎት ፡ ነበር ። በኋላም ፡ ለዚሁ ፡ አገር ፡ አሜሪካ ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ተሰጠው ፡ በዚህ ፡ የተነሣ ፡ አገሩን ፡ የእስፓኞ ፡ መንግሥት ፡ ይዞት ፡ ብዙ ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ መሠረተበት ። አገሩም ፡ ብዙ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ስለሚገኝበት ፡ እስፓኞ ፡ ሀብታም ፡ ሆና ፡ ብዙ ፡ መርከቦች ፡ እየሠራች ፡ ኃይሏ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ። እንግሊዞች ፡ ግን ፡ የእስፓኞ ፡ መርከቦች ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ጭነው ፡ ሲመጡ ፡ እየጠበቁ ፡ ይዘርፏቸው ፡ ጀመር ።

የእስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ ክሪስቶፍ ፡ ኮሎምብን ፡ በመርዳቱ ፡ ካሜሪካ ፡ አገር ፡ የተገኘውን ፡ ሀብት ፡ ቢወስድ ፡ የተገባ ፡ ነገር ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ብቻውን ፡ እንዲበላ ፡ ዘንድ ፡ ሌሎቹ ፡ በሰላም ፡ ሊተውት ፡ አልፈቀዱም ።

በመጨረሻ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋር ፡ የመርከብ ፡ ጦርነት ፡ አድርገው ፤ በውጊያው ፡ ሰዓት ፡ ትልቅ ፡ ማዕበል ፡ ተነሥቶ ፡ አርማዳ ፡ የሚባሉትን ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ ይፈሩ ፡ የነበሩትን ፡ የእስፓኝን ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ አጠፋቸው ። በዓለም ፡ ላይ ፡ ክብሩዋ ፡ ከሁሉም ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ይታይ ፡ የነበረው ፡ የእስፓኝ ፡ አገር ፡ ቅስሟ ፡ ተሰብሮ ፡ እንግሊዝ ፡ ግን ፤ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያለች ፡ ሄዳ ፡ አሁን ፡ ካለችበት ፡ ደረጃ ፡ ደረሰች ።

ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ በአንቲይና ፡ በብሬዚል ፡ አገሮች ፡ በሰፊው ፡ እንዲሠራ ፡ ለታቀደው ፡ የጥጥና ፡ የሸንኮር ፡ አገዳ ፡ አታክልት ፡ ሥራ ፡ በቂና ፡ ብርቱ ፡ የሆኑ ፡ ሠራተኞች ፡ ማግኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ። ስለዚህ ፡ በአንቲይና ፡ በብሬዚል ፡ ኋላም ፡ በሰሜን ፡ አፍሪካ ፡ ክፍል ፡ በሚገኙት ፡ የእንግሊዝ ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ጥቁሮች ፡ ባሮች ፡ ከአፍሪካ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ እያሻገሩ ፡ ለማሠራት ፡ ይወስዱቸው ፡ ጀመር ። ከአፍሪካ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ባሮች ፡ የሚያስተላልፉባቸውም ፡ ብዙ ፡ መንገዶች ፡ ተከፈቱ ፡ ከጊኔ ፡ ወደ ፡ ፖርቱጋል ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ እስፓኝ ፡ አገር ፡ እያዘዋወሩ ፡ ባሮች ፡ የሚሸጡ ፡ ብዙ ፡ ነጋዴዎች ፡ ተነሡ ።

በአፍሪካ ፡ የባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ አገሮች ፡ እየመጡ ፡ የአፍሪካን ፡ ሰዎች ፡ በሰንሰለት ፡ እያሠሩ ፡ ወስደው ፡ ባሮች ፡ ማድረግ ፡ የጀመሩ ፡ የፖርቱጋል ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንግሊዞች ፤ ፈረንሣዮች ፤ የእስፓኝ ፡ ሰዎች ፡ በጠቅላላውም ፡ ባለ መርከብ ፡ የሆኑ ፡ የአውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ መጥፎ ፡ አብነት ፡ ተከተሉ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሕዝቡ ፡ ከባሕር ፡ ጠረፍ ፡ አቅራቢያ ፡ ከሚገኘው ፡ አገር ፡ እየለቀቀ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ርቆ ፡ ተቀመጠ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ባርያ ፡ ፈንጋዮች ፡ ከገቡበት ፡ ቦታ ፡ እየገቡ ፡ ሕዝቡን ፡ በባርያ ፡ ፈንጋይነት ፡ እያፈኑ ፡ ለመውሰድ ፡ አላገዳቸውም ።

በጣም ፡ የሚያስገርመው ፡ ደግሞ ፡ የጦር ፡ ምርኮኞችና ፡ ወንጀለኞች ፡ የሆኑትን ፡ ያገሩን ፡ ሕዝብ ፡ ለአውሮፓውያን ፡ ባሮች ፡ እያደረገ ፡ ሊሸጥ ፡ ይችላል ። አውሮፓውያንም ፡ ለዚህ ፡ ዋጋ ፡ የጌጥ ፡ ዕቃ ፡ ይሰጣሉ ፡ የሚል ፡ የንግድና ፡ የሰላም ፡ ስምምነት ፡



የተባለ ፡ ውል ፡ በመፈራረም ፡ በአውሮፓውያንና ፡ በአፍሪካ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ለባርያ ፡ ንግድ ፡ መሠረት ፡ የሆነ ፡ ግንኙነት ፡ ተበጀ ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ባርያ ፡ ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ ሰውን ፡ ከወንጀለኛ ፡ የሚያስቈጥረው ፡ ጥፋት ፡ በእነዚያ ፡ አገሮች ፡ የበዛ ፡ ሆነ ። ወንጀለኛ ፡ የተባለውም ፡ በወንጀሉ ፡ ሥራ ፡ ብቻውን ፡ መቀጣቱ ፡ ቀርቶ ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ሁሉ ፡ አብረው ፡ ተቀጪዎች ፡ እየሆኑ ፡ ይሸጡ ፡ ጀመር ። ያገሩ ፡ ሹሞች ፡ አረቄና ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጠጥ ፡ ሲያምራቸው ፡ ላውሮፓውያን ፡ ባሮች ፡ እየሸጡ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ሕዝባቸውን ፡ በግፍ ፡ ጥፋተኛ ፡ በማድረግ ፡ እያፈሱ ፡ ይሰጧቸዋል ። ከአፍሪካ ፡ እየወሰዱ ፡ ጥቁሮችን ፡ ባሮች ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ እያስተላለፉ ፡ በመሸጥ ፡ አውሮፓውያን ፡ የሠሩት ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እየተስፋፋ ፡ ሄደ ። በ፲፯፻፹፰ ፡ ዓ. ም. ከአፍሪካ ፡ የወጡት ፡ ባሮች ፡ መቶ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ናቸው ። በተከተሉት ፡ አምስት ፡ ዓመታትም ፡ ውስጥ ፡ ይህንኑ ፡ ያህል ፡ መሆናቸው ፡ ተገምቷል ።

ሻርልክ ፤ ወይም ፡ ሻርል ፡ አምስተኛ ፡ የሚባለው ፡ የእስፓኝ ፡ ንጉሥ ፡ በ፲፭፻፲፰—፲፱—፳ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በሦስቱ ፡ ዓመታት ፡ እየታደሱ ፡ ተከታትለው ፡ በወጡት ፡ አዋጆች ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ፡ ከሚገኙት ፡ ሃይቲ ፤ ኩባ ፤ ጀማይካ ፤ ፓርቶሪኮ ፡ ወደሚባሉት ፡ የእስፓኝ ፡ ግዛቶች ፡ ባመት ፡ ባመቱ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ጥቁሮች ፡ ባሮች ፡ እያገባ ፡ እንዲሸጥ ፡ ላ ፡ ብሬዛ ፡ ለሚባል ፡ የፍላንድር ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ፈቀደለት ። ከእስፓኝ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሃይቲ ፡ ጥቁሮቹ ፡ ባሮች ፡ መግባት ፡ የጀመሩት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በ፲፭፻፲፰ ፡ ዓ. ም. ነው ። በመጀመሪያ ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ ሞኖፖል ፡ የያዘች ፡ እስፓኝ ፡ ነበረች ። ቀጥሎ ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ ሲከናወን ፡ ከነጋዴዎች ፡ ላይ ፡ በያንዳንዱ ፡ ባርያ ፡ ቀረጥ ፡ እየተቀበለ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ እነዚህ ፡ ባሮች ፡ ባሜሪካ ፡ አገር ፡ ሲገቡ ፡ ያገሩ ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑት ፡ ሕንዶችን ፡ በእነሱ ፡ እግር ፡ ጥቁሮች ፡ ስለ ፡ ተተኩላቸው ፡ ገንዘብ ፡ እያስከፈለ ፡ ስለሆነ ፡ ነፃ ፡ የሚለቃቸው ፡ በዚህ ፡

ሥራ ፡ ተጠቅሞበት ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ላይ ፡ የቅኝ ፡ አገሮቹን ፡ የሚያለማለት ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ ባሮች ፡ የሚገዙትን ፡ ባለርስቶች ፡ ባንዳንድ ፡ ባርያ ፡ ከሠላሳ ፡ ዱካ ፡ በላይ ፡ ቀረጥ ፡ ያስከፍላቸው ፡ ነበር ። በአንቲይና ፡ በብሬዚል ፡ የሸንኮር ፡ አገዳ ፡ አትክልት ፡ ሥራ ፡ እየተስፋፋ ፡ ሲሄድ ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ እየበዛ ፡ ሄዷል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የሸንኮር ፡ አገዳ ፡ በገባበት ፡ አገር ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ ይከተላል ፤ እየተባለ ፡ ተተርቷል ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ያውሮፓውያን ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ በአሜሪካ፡ አገር ፡ እየጨመረ ፡ የሸንኮር ፡ አገዳ ፡ የመትከል ፡ ሥራም ፡ እየተስፋፋ፡ ሲሄድ ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ ጉዳይ ፡ ባውሮፓ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ሆነ ። ብዙ፡ ነጋዴዎች ፡ ከእነዚሁ ፡ የጀርመንና ፡ የጀኖቫ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የሆኑ ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ባርያ ፡ ንግድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ፡ ውል ፡ እየተዋዋሉ ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ፖርቱጋሎች ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ንግድ ፡ መሆኑን ፡ እየተረዱት ፡ ስለሄዱ ፡ ሞኖፖሉን ፡ ራሳቸው ፡ ይዘው ፡ ይሠሩበት ፡ ጀመር ። ይሁን ፡ እንጂ፡ ባለመርከብ ፡ የሆኑ ፡ በአትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ላይ ፡ የሚዘዋወሩ ፡ ሕዝቦች ፡ ከእነዚሁም ፡ ፈረንሳዮች ፡ እንግሊዞችና ፡ ሆላንዶች ፡ ግማሾቹ ፡ በወምበዴነት ፡ ግማሾቹ ፡ በኮንትረባንድ ፡ ብዙዎቹም ፡ በደንብ፡ ከመንግሥት ፡ ጋር ፡ እየተዋዋሉ ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ፡ ወደሚገኙት ፡ ግዛቶቻቸው ፡ እየወሰዱ ፡ ባሮች ፡ ይሸጡ ፡ ጀመር ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ለምሳሌ ፡ እንግሊዞች ፡ ጃማይካ ፡ በምትባለው ፡ ደሴት ፡ ያደርጉት ፡ እንደነበረው ፡ የእስፓኛ ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ከሆኑት ፡ አጠገብ፡ የሚወስዷቸውን ፡ ባሮች ፡ አከማችተው ፡ እያቆዩ ፡ ኋላም ፡ ከእስፓኛ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ እያገቡ ፡ ይሸጧቸው ፡ ነበር ።

የኢጣሊያ ፡ ትሬካኒ ፡ ኤንሲክሎፔዲያ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ስታቲስቲክ ፡ ይሰጠናል ፤ ናንት ፡ ከምትባለው ፡ የፈረንሳዊ ፡ ወደብ ፡ ብዙ ፡ መርከቦች ፡ መጠጥና ፡ ጨርቃጨርቆች ፡ ሌላም ፡ ይህን፡ የመሰለ ፡ ርካሽ ፡ የሆነ ፡ ሸቀጥ ፡ ጭነው ፡ በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ ጊኔ ፡ ከሚባለው ፡ አገር ፡ አግብተው ፡ ይህን ፡ የጫኑትን ፡ ሸቀጥ፡ በለውጥ ፡ ብዙ ፡ ባሮች ፤ ይገዙበትና ፡ ባሮቹን ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ ይወስዷቸዋል ፤ እዚያም ፡ በአንቲይና ፡ በብሬዚል ፡ ከሚ



ኖሩ ፡ ነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ ተስማምተው ፡ ይሸጧቸውና ፡ ስለዋጋው ፡ ስኳርና ፡ ትንባሆ ፡ ተቀብለው ፡ ወደ ፡ ናንት ፡ ይመለሳሉ ። በዚህ ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ የሚያገኙት ፡ ጥቅም ፡ ብዙ ፡ ነበር ፤ ለምሳሌ ፡ በጊኔ ፡ አገር ፡ አንዱን ፡ ባርያ ፡ በዕቃ ፡ ለውጥ ፡ ሲገዙት ፡ ከአርባ ፡ እስከ ፡ ሃምሳ ፡ የሆላንድ ፡ ፍሎሪን ፡ ይከፍሉበታል ፤ አሜሪካ ፡ አገር ፡ ሲገቡ ፡ አንዱን ፡ ባርያ ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ፍሎሪን ፡ ይሸጡታል ፤ የሚቀበሉትም ፡ ስኳርና ፡ ትንባሆ ፡ ስለሆነ ፡ አውሮፓ ፡ ወስደው ፡ ሲሸጡት ፡ ብዙ ፡ ያተርፉበት ፡ ነበር ።

ከ፲፯፻፵፩ ፡ እስከ ፡ ፲፯፻፵፫ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ ባራቱ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ከናንት ፡ ወደብ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ በድምሩ ፡ ባመት ፡ ባመቱ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ መርከቦች ፡ ዘጠኝ ፡ ሺህ ፡ ባሮች ፡ ወስደው ፡ በመሸጥ ፡ ተመላልሰዋል ። ይህ ፡ ባንዲት ፡ የፈረንሳይ ፡ ወደብ ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ ነው ። በቀሩት ፡ በፈረንሳይ ፡ ወደቦችና ፡ በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ የተደረገው ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ይበልጣል ።

እንግሊዝ ፡ ደግሞ ፡ በኡትሬክ ፡ (Utrecht) ላይ ፡ በፈረንሣይ ፡ በእንግሊዝ ፡ በእስፓኛና ፡ በሆላንድ ፡ መካከል ፡ የተፈረመው ፡ ውል ፡ በሰጣት፡ የጥቅም ፡ መብቶች ፡ መሠረት ፡ ወደ ፡ ቅኝ ፡ አገሮቿ ፡ ከምትልካቸው ፡ ባሮች ፡ ሌላ ፡ ወደ ፡ እስፓኛ ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ እየወሰደች ፡ ትሸጥ ፡ ስለነበር ፡ በሰላሣ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ባሮች ፡ ሸጣለች ። የሰሜን ፡ ባሕር ፡ ኩባንያ ፡ የሚባል ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሞኖፖሉን ፡ ወስዶ ፡ ሐያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ነግዶበታል ። የሚበልጠውንም ፡ አክሲዮን ፡ በዚህ ፡ ንግድ ፡ ውስጥ ፡ የያዙት ፡ የእስፓኛ ፡ ንጉሥና ፡ የእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ነበሩ ። ከሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በባርያ ፡ ነግዷል ። በ፲፯፻፸፱ ፡ ዓ. ም. ይህ ፡ ሞኖፖል ፡ ቀርቶ ፡ የእንግሊዝ ፡ ዜጎች ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ በነፃ ፡ እንዲነግዱ ፡ ስለተፈቀደላቸው ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ ይበልጥ ፡ እየተስፋፋ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ ረዳ ።

መጀመሪያ ፡ ብሪስቶል ፡ በሚባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ወደብ ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ በሰፊው ፡ መሠራት ፡ ጀመረ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ሊቨርፑል ፡

የሚባለው ፡ ወደብ ፡ በዚህ ፡ ንግድ ፡ የበለጠ ፡ ደረጃ ፡ አገኘ ፤ በ፲፯፻፸፩ ዓ. ም. ከሊቨርፑል ፡ ብቻ ፡ መቶ ፡ ሰባት ፡ መርከቦች ፡ ሐያ ፡ ስምንት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ባሮች ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ ወስደዋል ። በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ከብሪስቶል ፡ ባሮች ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ የሄዱ ፡ መርከቦች ፡ ቍጥራቸው ፡ ሃያ ፡ ሦስት ፡ ከሎንዶን ፡ አምሳ ፡ ስምንት ፡ ናቸው ።

በሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ በሚገኙት ፡ የእንግሊዝ ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ በ፲፯፻፲፮ ዓ. ም. የነበሩት ፡ ጥቁሮች ፡ ባሮች ፡ ቍጥራቸው ፡ ስድሳ ሺህ ፡ ሲሆን ፡ በ፲፯፻፶፬ ፡ ዓ. ም. ከሁለት መቶ ስድሳ ፡ ሺህ ፡ በ፲፯፻፸፬ ፡ ዓ. ም. ከሰባት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ስድሳ ፡ ዘጠኝ ፡ ደርሷል ። በአሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ መቶ ዓመት ፡ ማለቂያ ፡ ላይ ፡ ከአሜሪካ ፡ አገር ፡ ገብተው ፡ ሊሸጡ ፡ የተወሰዱት ፡ ባሮች ፡ ቍጥራቸው ፡ ከሦስት ፡ ሚሊዮን ፡ በላይ ፡ ሆኗል ። ከእነዚሁ ፡ መካከል ፡ በየመንገዱ ፡ የሞቱት ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሺህ ፡ መሆናቸው ፡ ተገምቷል ። በሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በባርያ ፡ ፈንጋይነት ፡ ከገራቸው ፡ በግድ ፡ ተይዘው ፡ እየወጡ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ የተሸጡት ፡ ባሮች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ጠቅላላ ፡ ድምራቸው ፡ ባይታወቅ ፡ ከዚህ ፡ ቍጥር ፡ በላይ ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ።



## የሄዱበት ፡ ሁኔታ ።

እነዚህን ፡ ጥቍሮች ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ከገራቸው ፡ እያወጡ ፡ እንደወሰዷቸው ፡ ስንመለከተው ፡ እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ባርያ ፡ ፈንጋዮች ፡ ሌሊት ፡ ባገሩ ፡ ተወላጆች ፡ መንደር ፡ ገብተው ፡ ቤታቸውን ፡ እሳት ፡ እየተኰሱበት ፡ ሸሽተው ፡ ከቤታቸው ፡ ሲወጡ ፡ እያባረሩ ፡ ያድኗቸዋል ፤ ሰውነቱ ፡ ብርቱ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ ሊብር ፡ ስቴርሊንግ ፡ ይሸጥ ፡ ነበር ። ለመጠበቅና ፡ በመንጋ ፡ ለመንዳት ፡ እንዲመቻቸው ፡ ብዙዎቹን ፡ ባሮች ፡ በረጅም ፡ ሠንሰለት ፡ አንድነት ፡ አያይዘው ፡ በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ አጠገብ ፡ በሚገኘው ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ በሚያቃጥል ፡ የበረሃ ፡ አሸዋ ፡ ላይ ፡ ይነዷቸዋል ፤ ሕጻናቶችንም ፡ ከወላጆቻቸው ፡ ጋር ፡ እግራቸው ፡ እየተቃጠለ ፡ ደም ፡ ሲያዘንብ ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ አንድነት ፡ ይነዷቸዋል ፡ ብዝዎቹም ፡ እየደከሙ ፡ በየመንገዱ ፡ ስለሚሞቱ ፡ አፅማቸው ፡ እየተከሰከሰ ፤ ባለፉበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ሆኖ ፡ ረግፏል ፤ የተረፉትም ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መከራ ፡ ተጉዘው ፡ ይደርሱ ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ጥቁሮች ፡ ትንሽ ፡ በሆነች ፡ መርከብ ፡ ተፋፍገው ፡ እየተጫኑ ፡ የበቃ ፡ ምግብ ፡ ሳያገኙ ፡ እየተራቡ ፡ ውሃ ፡ ብቻ ፡ እየጠጡ ፡ ማናቸውም ፡ የጤንነት ፡ ጥበቃ ፡ ሳይደረግላቸው ፡ እየቀረ ፡ ብዙዎቹ ፡ በመንገድ ፡ ይሞታሉ ፤ የተረፉት ፡ ደግሞ ፡ ከአሜሪካ ፡ አገር ፡ ሲገቡ ፡ በሥራ ፡ ብዛት ፡ ከመገፋትና ፡ ከአየሩም ፡ አለመስማማት ፡ የተነሣ ፡ ከመካከላቸው ፡ ብዝዎቹ ፡ ሞተዋል ፤ የአታክልቱንም ፡ ሥራ ፡ የሚአሠሩዋቸው ፡ ሰዎች ፡ የተቻላቸውን ፡ ያህል ፡ በድካማቸው ፡ እንዲጠቀሙ ፡ ከመጣጣር ፡ በቀር ፡ ለጤንነታቸውና ፡ ለኑሮአቸው ፡ በጭራሽ ፡ ስለሚያስቡላቸው ፡ በፈቃዱት ፡ አኳኋን ፡ እንደከብት ፡ ያሠሩዋቸዋል ፡ እንጂ ፡ መንግሥት ፡ በማነኛውም ፡ ረገድ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ግፍ ፡ ለመጠባበቅ ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በዳኝነት ፡ ረገድ ፡ አይቆጣጠራቸውም ፡ ነበር ። ብዙዎቹ ፡ ባሮች ፡ ከመካከላቸው ፡ ከመከራቸው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ሞተዋል ፤ ግማሾቹም ፡ እየጠፉ ፡ ግማሾቹም ፡ አንገዛም ፡ እያሉ ፡ በጌቶቻቸው ፡ ላይ ፡ እያመፁ ፡ በየጊዜው ፡ ሁከት ፡ አንሥተዋል ። ይህን ፡ የመሰለው ፡

ነገር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚደርሰውም ፡ አዲሶች ፡ ባሮች ፡ ካገራቸው ፡ እየተያዙ ፡ ገና ፡ ሲደርሱ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ ቀድመው ፡ ከእነሱ ፡ በፊት ፡ የቆዩዋቸው ፡ ባሮች ፡ የሚሠሩባቸውን ፡ ግፍና ፡ ባኗኗራቸውም ፡ ያለባቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መከራ ፡ ሲያጫውቷቸው ፡ በነፃነት ፡ ይኖሩ ፡ ከነበሩበት ፡ አገራቸው ፡ ወጥተው ፡ የሚጠብቃቸውን ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ የመከራ ፡ ቀንበር ፡ ሲረዱት ፡ ከሚሰማቸው ፡ ሐዘንና ፡ ተስፋ ፡ መቁረጥ ፡ የተነሣ ፡ ነበር ።

ባሮች ፡ ግፍ ፡ ሲበዛባቸው ፡ ከጌቶቻቸው ፡ ዘንድ ፡ እየኰበለሉ ፡ ስለሚጠፉ ፡ ባርያ ፡ ከቤቱ ፡ አስገብቶ ፡ ያሳደረ ፡ የሚበላውና ፡ የሚጠጣው ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ በማንኛውም ፡ አኳኋን ፡ እርዳታ ፡ ያደረገለት ፡ ሰው ፡ የሚቀጣ ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳስብ ፡ አዋጅ ፡ ወጣ ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ገንዘብ ፡ እየተቀበሉ ፡ የኰበለለ ፡ ባርያ ፡ ተከታትለው ፡ የሚይዙና ፡ ይህንኑ ፡ ሥራቸው ፡ አድርገው ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። እነሱም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚያደርጉት ፡ መጥፎ ፡ ልማድ ፡ ነበራቸው ። ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ያሠለጠኑዋቸው ፡ ውሾች ፡ ስላሉዋቸው ፡ በጠረን ፡ እየፈለጉ ፡ የኰበለለውን ፡ ባርያ ፡ ይይዙታል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሰዎቹ ፡ ቶሎ ፡ ደርሰው ፡ ያላስጣሉዋቸው ፡ እንደሆነ ፡ ውሾቹ ፡ ባሮቹን ፡ ገነጣጥለው ፡ ይበሏቸዋል ።

በአሜሪካ ፡ አገር ፡ ይልቁንም ፡ የባርያ ፡ ዋና ፡ ገበያ ፡ በመሆኗ ፡ በታወቀችው ፡ ባዲሷ ፡ ኦርሊያን ፡ ከተማ ፡ የሚሸጡ ፡ ባሮች ፡ የሚከማቹበትን ፡ መጋዘን ፡ የጐበኘ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ያይ ፡ ነበር ። ላንድ ፡ ጌታ ፡ የተገዙ ፡ ባሮች ፡ ተጋብተው ፡ ልጆችም ፡ ወልደው ፡ ሲኖሩ ፡ ጌታቸው ፡ ሲሞት ፡ ወራሾቹ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይሸጡዋቸዋል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ጌታቸው ፡ ይከሥርና ፡ ዕዳ ፡ ሲገባ ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ሲቸግረው ፡ ከባሮቹ ፡ ሕፃኖቹ ፡ ልጆች ፡ ከናታቸው ፡ ባል ፡ ከሚስቱ ፡ እየተነጠሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይሸጣሉ ። የባርያ ፡ ነጋዴ ፡ የሆነ ፡ በጅምላ ፡ እየገዛ ፡ ብዙ ፡ ዋጋ ፡ እንዲያወጡለት ፡ ከቀለባቸው ፡ በኋላ ፡ ከገበያ ፡ ያወጣቸዋል ። እስኪሸጡም ፡ ድረስ ፡ ከመካከላቸው ፡ ( ሙዚቃ ) የሚጫወትና ፡ ዘፈን ፡ የሚያውቅ ፡ ፈልጎ ፡ እንዲዘፍኑና ፡ እንዲጨፍሩ ፡ ያደርጋቸዋል ። ባሮቹም ፡



ያልተጫወቱ ፡ እንደሆነ ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የሚገዛቸው ፡ ሰው ፡ ጠፍቶ ፡ ጨካኝና ፡ ኃይለኛ ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዳይገቡ ፡ መልካም ፡ ጌታ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ መከራቸውን ፡ ማሰብ ፡ ትተው ፡ ያለውዴታቸው ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር ።